WIEGO

FITH·IDWF·FITD



# በ ዓለም ሥራ ድርጅት ስምምነት 189 ላይ የእርስዎ የተግባር መሳሪያ -

# የዓለም ሥራ ድርጅት ስምምነት 189 ላይ የእርስዎ የተግባር መሳሪያ (ቱልኪት)

## የቤት ሰራተኞች ስምምነት (አፍሪካ ክልል)

**የ WIEGO-IDWF እትም**

**የታተመበት ቀን**

**አክቶበር 2018**

በ Women in Informal Employment: Globalizing and Organizing (WIEGO) የታተመ
WIEGO በበጎ ፈቃደኝነት የሚሰራ ዋስትናው የተወሰነ ነው – ኩባንያ ቁ. 6273538፣ የተመዘገበበት የበጎ ፍቃደኝነት ቁ. 1143510

WIEGO Limited, 521 Royal Exchange
Manchester, M2 7EN, United Kingdom
www.wiego.org

ቅጂ መብት © WIEGO

ባለቤትነቱ እውቅና እስከተሰጠው ድረስ ይህ ሪፖርት ለትምህርት እና ለማስተባበሪያ አላማዎች ሊባዛ ይችላል።

## ይዘት


**መግቢያ ........................................................................................................ 2**

በነዚህ የተግባር መሣሪያዎች ውስጠ ያሉ ቃላት እና ሀረጎች እና ትርጉማቸው ................................ 4

**ክፍል 1፡የዓለም ሥራ ድርጅት ስምምነት 189 – ምንድነው? ....................................................... 6**

ስምምነት189 የሚተገበረው ለማን ነው? ............................................................................ 7

ስምምነት189 ያወጣው ዝቅተኛ መስፈርቶች ምንድናቸው? ..................................................... 7

**ክፍል 2፡ ማጽደቅ ምንድነው ለምንስ አስፈላጊ ሆነ? ................................................................. 12**

የስምምነት ማጽደቅ ማለት ምን ማለት ነው? ...................................................................... 12

ስምምነት189 ለመጽደቅ አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው? ......................................................... 13

**ክፍል 3፡ ስምምነት 189 ለቤት ሰራተኞች እንዴት እውን ሊሆን ይችላል? ...................................... 14**

ደረጃ 1፡ ሃገርዎ ስምምነት189ን አጽድቀው እንደሆነ ይወቁ ................................................... 14

ደረጃ 2፡ በህጋችሁ ውስጥ ክፍተት መኖሩን ለማወቅ ይህንን የማረጋገጫ ዝርዝር ይጠቀሙ ................ 15

ደረጃ 3፡ ስምምነት 189 ን የቤት ሰራተኞች ስለ ስምምነት 189 አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይጠቀሙበት 19

ማጠቃለያ፡ ስምምነት 189 ን እውን ማድረግ ...................................................................... 25

**ክፍል 4፡ የቅጥር ሞዴል ውል................................................................................................ 27**

ለቤት ሰራተኞች አስተባባሪዎች እና አስተማሪዎች ምክሮች...................................................... 27

ለቀጣሪዎች እና ለቤት ሰራተኞች ምክሮች........................................................................... 27

አባሪ 1፡ በምክረ ሃሳበ 201 ላይ አማራጭ አንቀጾች ............................................................. 33

አባሪ 2፡ በብሄራዊ ሞዴል ውሎች አማራጭ አንቀጾች.............................................................. 35

አባሪ 3፡ ወርሃዊ የጊዜ መቆጧተሪያ እና የክፍያ ማረጋገጫ ደረሰኝ ................................................ 37

**ክፍል 5፡ ሌሎች መጠቀም የሚችሏቸው ግባአቶች .................................................................... 39**

በ ስምምነት189 ላይ ያሉ ግብአቶች .................................................................................. 39

ማስተባበር ላይ ያሉ ግብአቶች ......................................................................................... 40

**ተጨማሪ መግለጫ፡ ያለም ሥራ ድርጅት ምክረሐሳብ ቁ. 201 ምንድነው?........................................ 41**

# መግቢያ

በአለም ላይ ባሉ ሁሉም ሀገራት የቤት ሰራተኞችን ያገኛሉ - እየተከፈላቸው በሰው ቤት ውስጥ የሚሰሩ ሰዎች (አብዛኛውን ጊዜ ሴቶች)።

እንደ አስተባባሪ፣ የቤት ሰራተኞችን በማስተባበር ብዝበዛቸውን እንዲያስቆሙ መርዳት ይፈልጉ ይሆናል፡

- አብዛኞቹ ዝቅተኛ ክፍያ የሚያገኙ፣ ደካማ የመስሪያ ሁኔታ እና አብዛኛውን ጊዜ ያለ ቅጥር ውል የሚሰሩ ናቸው።
- አብዛኞቹ መንግስታት የቤት ሰራተኞችን እንደ ሰራተኛ አይቆጥሯቸውም።
- የሌላ ሃገር ሰው ከሆኑ ስራቸውን ትተው ሌላ ስራ ማግኘት በጣም ይከብዳቸዋል።
- ሁልጊዜ በሚባል ደረጃ በጣም ብዙ ሰአታት ከትንሽ እረፍት ጋር ይሰራሉ።
- በራሳቸው ስለሚሰሩ፣ አሰሪዎቻቸው በቀላሉ ሊያባሯቸው ወይም ሊያሰቃዩዋቸው ይችላሉ።

የቤት ሰራተኞችን በሚያስተባብሩበት ወቅት ተግዳሮቶች ሊገጥምዎት ይችላል፡

- አብዛኞቹ አሰሪዎቻቸውን ስለሚፈሩ ህብረትን ወይም የሰራተኞች ትብብርን ከተቀላቀሉ ስራቸውን ሊያጡ እንደሚችሉ ይናገራሉ።
- የአብዛኞቹ ስራ በአሰሪዎቻቸው መኖሪያ ቤት ስለሆነ - በህብረት ከሆኑ፣ አሰሪዎቻቸው እንዳያባሯቸው እና ቤታቸውን እንዳያጡ ይፈራሉ።
- አንዳንዶቹ ከሌላ ሃገር የመጡ ናቸው ( አብዛኛውን ጊዜ ያለ ህጋዊ ወረቀት)። ህብረቶችን ወይም የሰራተኛ ትብብርን ተቀላቅለው አሰሪያቸውን መጋፈጥ እስከ መባረር ሊያደርሳቸው ይችላል።
- ረጅም የስራ ሰአታቸው እና በራሳቸው መስራታቸው እርስዎን እንዲያገኙ ወይም ስብሰባዎችን ለመካፈል እንዲከብዳቸው ሊያደርግ ይችላል።



እነዚህ ተግዳሮቶች ቢኖሩም በአለም ዙሪያ ያሉ የቤት ሰራተኞች እየተባበሩ እና ለእውቅና እየታገሉ እና እንደ ሰራተኛ መብታቸውን እያስከበሩ ነው። የእርስዎ ተሞክሮ ይህን ይመስላል? *አንድ አንድ ጊዜ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ሊሰማዎ ይችላል። ነገር ግን ተስፋ አለ።*

በመጀመሪያ ግን ማን እንደሆንን እንንገርዎ። **እኛ Women in Informal Employment: Globalizing and Organizing**, በአጭሩ WIEGO ነን። አብረንም በአለም አቀፍ ያሉ የቤት ሰራተኛ ድርጅቶችን ከሚያግዘው ከዓለም አቀፍ የቤት ሠራተኞች ማኅበር ፌደሬሽን (International Domestic Workers' Federation) (IDWF) ጋር እንሰራለን። IDWF የቤት ሰራተኞች መብት ትግልን የሚመራ ሲሆን በ 54 ሃገሮች 67 አባል ድርጅቶች አሉት። WIEGO በተለይም ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የተቀጠሩ የሰራተኞች ህይወትን ሊያሻሽሉ የሚችሉ አለምአቀፍ ፖሊሲዎች ላይ ተጽእኖ ለማምጣት ይሞክራል:: እናም ድርጅቶቻቸውን ለማጠንከር ይረዳል። (ለተጨማሪ መረጃ በ **www.wiego.org** እና በ**www.idwfed.org** ያግኙን)።

ከ 10 አመት በላይ በአለም ዙሪያ ያሉ የቤት ሰራተኞች አለምአቀፍ ድርጅቶቻቸውን ሲገነቡ ቆይተዋል። እንደ ብሄራዊ የሰራተኛ ማህበራት ህብረቶች፣ አለምአቀፍ የሰራተኛ ማህበራት ህብረት አካላት፣ በተለይም አለምአቀፍ የምግብ፣ የግብርና፣ ሆቴል፣ ሬስቶራንት፣ አስተናጋጅ፣ ትምባሆ ህብረት እና የተባበሩት የሰራተኞች ፌደሬቲን (IUF) እና እንደ WIEGO ባሉ አጋዥ ድርጅቶች በመሳሰሉ አጋሮች ሲረዱ ነበር። እኛ ሁላችንም ከየሃገራችን የቤት ሰራተኞች ችግሮችን ተጋርተናል። አብረን በመስራትም፣ የቤት ሰራተኞችን በደንብ ለመጠበቅ ስልት ነድፈናል።

አንደኛው በጣም ጠቃሚ ስልት በአለም የስራ ድርጅት (International Labour Organization) ወይም ILO ተብሎ በሚጠራው ላይ ጫና መፍጠር ነው። በአለም የስራ ድርጅት (ILO) በአለም ላይ ካሉ ሁሉም ሀገሮች መንግስታት፣ የሰራተኛ ድርጅቶች እና የአሰሪ ድርጅቶች የተውጣጣ ሲሆን ቁልፍ ስራውም **በስምምነቶች እና ምክረሐሳቦች ላይ** መደራደር እና መቀበል ነው። እነዚህ የሰራተኛን ህግ የሚያስከብሩ አለምአቀፋዊ መስፈርቶች ሲሆኑ ሁሉም ሃገሮች መብቶቹን እውን ለማድረግ አጽድቀው ብሄራዉ ህግ እንዲወጡ የሚያደርግ ነው። እኛም ILO ልዩ የሆነ የቤት ሰራተኞችን የሚጠብቅ **ስምምነት** እንደዲቀበል ፈልገን ነበር።

ቀላል ሂደት አልነበረ። እንደአውሮጳ አቆጣጠር በ 2010 እና 2011፣ የቤት ሰራተኞች እና አስተባባሪዎቻቸው የ ILO ኮንፍረንስ ላይ ተገኝተው ነበር፣ ይህም በተለይ በ IUF እና WIEGO የታገዘ ነበር። በተለያዩ ሃገራት ወኪሎች ድጋፍ አገኘን፣ በመጨረሻም ተሳካልን። የILO ስምምነት 189 ወይም የቤት ሰራተኛ ስምምነት ወይም በአጭሩ **C189** ን ተቀበለ።

ለስምምነቱ የነበረ ተግዳሮት አሁን የለም። አሁን ዋናው ስራ C189ን ለቤት ሰራተኞች እውን ማድረግ ነው።

WIEGO እና IDWF እንድ ላይ በመሆን ይህን የተግባር መሳሪያ (ቱልኪት) ጽፈዋል ይህም C189ን ለቤት ሰራተኞች እውን ለማድረግ የ IDWF ተባባሪዎችን ለመርዳት ነው። ይህንን የተግባር መሳሪያ ካረቀቅን በኋላ፣ አፍሪካ ውስጥ ካሉ 21 IDWF ተባባሪ ሃገራት ጋር ኬንያ ውስጥ ወርክሾፕ አዘጋጅተን ነበር። ከወርክሾፑ በኋላ፣ የ IDWF አጋሮችን እንዴት ይህን የተግባር መሳሪያ ማሻሻ፤ እንደምንችል ጥይቀናቸዋል። ተስፋ የምናደርገውም ይህ ቅስቀሳዎችን እንዲያግዝ፣ መንግስትን እንዲያስተምር እና ሰራተኞች እንዲረዱት እንዲያስተባበር እና C189ን እንዲያስተዋውቅ ነው። ይህ የተግባር መሳሪያ አምስት ክፍሎች አሉት፡

**ክፍል 1:** የዓለም ሥራ ድርጅት ስምምነት 189 – ምንድነው?

**ክፍል 2:** ማጽደቅ ምንድነው ለምንስ አስፈላጊ ሆነ?

**ክፍል 3:** ስምምነት 189 ለቤት ሰራተኞች እንዴት እውን መሆን ይችላል?

**ክፍል 4:** የቅጥር ሞዴል ውል

**ክፍል 5:** ሌሎች መጠቀም የሚችሏቸው ግባአቶች

# በዚህ የተግባር መሳሪያ (ቱልኪት) ውስጥ ያሉ ቃላት እና ሀረጎች እና ትርጉማቸው



**ልጅ**
ከ 18 አመት በታች የሆነ ሰው።



**የቤት ሰራተኛ**
በክፍያ በሰው ቤት ውስጥ የምትሰራ/የሚሰራ ሰው።

**አሰሪ**
የቤት ሰራተኛ ቀጥሮ የሚያሰራ ሰው

**ዓሥድ (አይ.ኤል. ኦ) (ILO)**
ዓለም ስራ ድርጅት (International Labour Organization) የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ነው። ILO የተቋቋመው እንደአውሮጳ አቆጣጠር በ 1919 ሲሆን ዋና መስሪያ ቤቱም ጄኔቫ፣ ስዊዘርላንድ ነው። ከ 187 አባል ሃገራት የመንግስታትን፣ የአሰሪዎችን እና የሰራተኞች ወኪሎችን አንድ ላይ ይሰበስባል። አንድ ላይም አባል ሃገራት መከተል ያለባቸውን የስራ መስፈርቶች ያወጣሉ። የእርስዎ ሃገር እዚህ ውስጥ ካለ በዚህ ይፈልጉ።
**http://www.ilo.org/public/english/standards/relm/country.htm**




**(አይ.ኤል. ኦ) ILO ስምምነት**
በ(አይ.ኤል. ኦ) የሰራተኞች፣ የመንግስታት እና የሰራተኞች ወኪሎች ስምምነቶችን ይቀርጻሉ። እነዚህ ስምምነቶች የሚባሉ ሲሆን እንደ አለም አቀፍ የስራ መስፈርቶች ይታያሉ። አባል ሃገራትም ራሳቸው ሃገር እንዲተገብሩት (እንዲቀበሉት) ይበረታታሉ

**አባል ሃገር**
የ(አይ.ኤል. ኦ) አባል የሆነ ሃገር



**ስደተኛ የቤት ሰራተኛ**
ከአገሩ ወጥቶ (ከተወለደበት ሃገር) በሰወአገር (የስራ ሃገር) የሚሰራ ሰራተኛ




**ማህበራዊ አጋሮች**
የአሰሪዎች እና የሰራተኞች ድረጅቶች፣ (የሚኖሩ ከሆነ) የቤት ሰራተኞች ድርጅቶች እና የቤት ሰራተኞች አሰሪዎች።



**የተባበሩት መንግስታት**
እንደአውሮጳ አቆጣጠር በ 1945 የተቋቋመ አለም አቀፋዊ ድርጅት። ከ 193 አባል ሃገራት ጋር አለም አቀፍ ሰላም እና ደህንነትን ለመጠበቅ ይሰራል። (አይ.ኤል. ኦ) የተባበሩት መንግስታት አካል ነው።

**የሰራተኞች ድርጅት**
የቤት ሰራተኞችን የሚያስተባብር ህብረት ወይም ስብስብ።

## ክፍል 1:

# ILO ስምምነት 189 – ምንድነው?




ILO ስምምነት 189 የጸደቀው እንደአውሮጳ አቆጣጠር በ 2011 ነው። ለቤት ሰራተኞች ተቀባይነት ያለው ስራን ለማስተዋወቅ ቢያንስ 5 የስራ መስፈርቶች አሉት። አንድ ሃገር ስምምነት189ን ካጸደቀ፣ በ ስምምነት189 ላይ እንደተገለጡት የስራ መስፈርቶችን ለማሳደግ ቃል ይገባል። የILO ስምምነት የሚመክረው ሃገራት ስምምነት189ን እንዲያጸድቁ እና ወደ ህግ እንዲቀየሩት ወይም እርሱን ተጠቅመው ያለውን ህግ እንዲያሻሽሉ ነው።

ILO ስምምነት189ን በተቀበለ ጊዜ አብሮም ለቤት ሰራተኞች ተቀባይነት ያለው ምክረሃሳብን ተቀብሏል። የ ILO ምክረሃሳብ ሃገራት የስራ ህጋቸውን ለመቅረጽ የሚረዳቸው መመሪያዎች ናቸው። ከስምምነት ጋር በማይመሳሰል መልኩ፣ ምክሮች መጽደቅ አያስፈልጋቸውም እና በአባል ሃገራት ላይ በግድ መፈጸም የለበትም። ምክረሃሳብ ቁ. 201 (ወይም R201) አባል ሃገራትን የስራ ህግ እና ፖሊሲያቸውን ከስምምነት189 ጋር እንዴት ማጣጣም እንዲችሉ ያግዛል።

**እርስዎም ምክረ-ሐሳብ 201ን በመጠቀም የእርስዎ መንግስት በተወሰኑ የ ስምምነት189 ክፍሎች ላይ ምን ማድረግ እንዳለበት ማስረዳት ይችላሉ። ተመሳሳይ ጉዳይን በተለያየ መንገድ የሚያስረዳውን እንደዚህ አይነት ጽሁፍን ይመልከቱ።**

**ትርጉም፡**

ILO ስምምነት፡ የአሰሪዎች፣ የሰራተኞች እና የመንግስታት ወኪሎች በየአመቱ በጁን ላይ በሚኖረው በዓለም የስራ ኮንፍረንስ (ILC) ላይ ይቀመጣሉ። አንድ ላይም፣ ወኪሎቹ ስምምነቶችን ያረቃሉ፣ ከእነዚህ አንዳንዶቹም ስምምነቶች ይባላሉ። ስምምነት ልዩ የሆነ የስምምነት አይነት ሲሆን የአለም የስራ መስፈርቶችን ያወጣል። አባል ሃገራት (የILO አባል የሆኑ ሃገራት) እንደሚያጸድቁት እና በየሃገራቸው እንደሚተገብሩት ይወስናሉ።
ሃገራቸውም እንዲያጸድቁት ብዙ ጊዜ በሰራተኞች ብዙ ቅስቀሳን ይፈልጋል።

ስምምነትን በመፈረም እና በማጽደቅ፣ ሃገራት የተወሰኑ ነገሮችን ለማድረግ ይወስናሉ። ILO ሃገራት የወሰኗቸውን እና ያጸደቋቸውን ስምምነቶች እያደረጉ መሆኑን የሚያረጋግጥበት መንገድ አለው። ILO ለአባል ሃገራት በየጊዜው ካጸደቁት ስምምነት ውስጥ ምን ምን እንዳልተገበሩ እና ሃገራዊ ህጎችንም ወደ ስምምነቱ ለማቅረብ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ይነግራል።

## ስምምነት189 የሚተገበረው ለማን ነው?

ስ189 ለሁሉም የቤት ሰራተኞች ይተገበራል፡

- ሙሉ ጊዜ ወይም ከፊል ጊዜ ቢሰሩም፤
- በሚሰሩበት ቤት ውስጥ የሚኖሩ ቢሆኑም፣ ወይም ሌላ ቦታ እየኖሩ ወደ ስራ የሚጓዙ ቢሆንም፤
- በሚኖሩበት ሃገር የሚሰሩ ቢሆንም ወይም እንደ ስደተኛ ሰራተኛ ቢሰሩም፤ እና
- ለአንድ ቤት ብቻ ቢሰሩም ወይም ብዙ ቤቶች ውስጥ ቢሰሩም።

አባል ሃገራት በሃገራቸው ያሉ ማህበራዊ አጋሮችን ካማከሩ በኋላ የተወሰኑ የሰራተኛ ክፍሎችን ላያካትቱ ይችላሉ።



## ስምምነት189 ያወጣው ዝቅተኛ መስፈርቶች ምንድናቸው?

እየንዳንዱ አባል ሃገር ማረጋገጥ ያለበት የቤት ሰራተኞች የሚከተሉትን እያገኙ መሆናቸውን ነው፡

1. ሀ. መሰረታዊ መብቶች
2. ለ. የተጻፈ የቅጥር ውል
3. ሐ. መሰረታዊ የስራ ሁኔታዎች
4. መ. የስራ ቦታ ደህንነት እና ጤንነት
5. ሠ. ማህበራዊ ደህንነት
6. ረ. አሰሪዎቻቸው ላይ ቅሬታ የማስገባት ስልጣን

እያንዳንዱ አባል ሃገር እርግጠኛ መሆን ያለበት፡

1. ሰ. ስደተኛ የቤት ሰራተኞች ጥበቃ እንዳላቸው
2. ሸ. የስራ ቅጠር ኤጀንሲዎች በመንግስት ቁጥጥር ስር መሆናቸውን

## 1. ስምምነት189 የሚሰጠው መሰረታዊ መብቶች ምንድ ናቸው?

- የቤት ሰራተኞች ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የመታየት እና ምቹ የሆነ የስራ ሁኔታ እንዲኖራቸው ማድረግ ( አንቀ. 6)።
- የቤት ሰራተኞች ያላቸው መብቶች:
  - እነርሱን በደንብ ይወክላል ብለው የሚያስቡት ድርጅት ጋር መቀላቀል ወይም፣ ምንም ከሌለ ራሳቸው መመስረት (የመሰብሰብ ነጻነት)፤ እና
  - ከአሰሪዎቻቸው ጋር መደራደር መቻል (አንቀ. 3(2)(a)፣ አንቀ. 3(3))።
- እድሜው ከ 15 አመት በታች የሆነ የትኛውም ልጅ የቤት ሰራተኛ ሆኖ መስራት አይችልም። እድሜው ከዝቅተኛው መጠን በላይ የሆነ ልጅ የሆነ ሰራተኛ መሰረታዊ ትምህርት እንዲጨርስ ወይም የስራ ስልጠና እንዲወስድ ሊፈቀድለት ይገባል (አንቀ. 3(2)( c)፣ አንቀ. 4)።

**አባል ሃገራት ማድረግ ያለባቸው ነገሮች:**

- ልጆች ጤናቸውን፣ ደህንነታቸውን እና ሞራላቸውን ሊጎዱ የሚችሉ የቤት ስራዎችን እንዳይሰሩ ማረጋገጥ።
- እድሜያቸው ከ 15 አመት በላይ የሆኑ ልጆች የቤት ሰራተኞች የሚሰሩበትን የስራ ሰአታት መገደብ፣ በምሽት እንዳይሰሩ ማድረግ፣ ከባባድ ስራዎችን እንዳይሰሩ ማድረግ።
- የልጆችን የስራ እና የኑሮ ሁኔታ ማየት።

- ማንም ሰው የቤት ሰራተኛ እንዲሆን መገደድ የለበትም (አንቀ. 3(2)(b))።
- የትኛውም የቤት ሰራተኛ በስራ ቦታ ላይ መገለል ሊደርስባቸው አይገባም (አንቀ.በ3(2)(d))።
- አባል ሃገር ማድረግ ያለባቸው ነገር:
  - የቤት ሰራተኞችን ከበደል፣ ከትንኮሳ እና ከሁከት መጠበቅ (አንቀ. 5)።
  - ሰራተኞች በሚሰሩበት ቦታ መኖር ወይም ከሚሰሩበት ቦታ ውጪ ለመኖር ከአሰሪዎቻቸው ጋር መደራደር እንዲችሉ ማረጋገጥ (አንቀ. 9(a))፤
  - ሰራተኞች የጉዞ እና የማንነት መግለጫ ሰነዶቻቸውን ራሳቸው ጋር መያዝ እንዲችሉ ማረጋገጥ (አንቀ. 9(c));
  - **ቤት-ውስጥ የሚኖሩ የቤት ሰራተኞች** የሚከተሉትን ማግኘታቸውን አረጋግጡ፡
    i. የግል ሕይዋታቸውን የሚያከብር ምቹ የሆነ የስራ ሁኔታዎች እንዳላቸው (አንቀ. 6)።
    ii. የእረፈት ጊዜያቸውን ወይም የውጪ ፍቃዳቸውን በቤት ውስጥ እንዲያሳልፉ አለመገደዳቸውን (አንቀ. 9(b))፤
    iii. ተጠባባቂ ሰአትን የሚቆጣጠር የህግ ከለላ ማግኘት (አሰሪው ከፈለጋቸው ማገኘት ያለባቸውን ጥቅም እንዲያገኙ) (አንቀ. 10(3))።

**አባል ሃገራት ማድረግ ያለባቸው ነገሮች:**

- የቤት ሰራተኞች የራሳቸውን ድርጅቶች ማቋቋም እንዲችሉ ወይም ሌሎች ድርጅቶችን በቀላሉ መቀላቀል እንዲችሉ የሚያደርግ ህግ እና ሂደት መኖሩን እርግጠኛ መሆን።
- የቤት ሰራተኛ ድርጅቶችን እንዲጠነክሩ ማገዝ።

**አባል ሃገራት ማድረግ ያለባቸው ነገሮች:**

- የቤት ራተኞች የህክምና መረጃን ለመጠበቅ ህግ ማውጣት እና ለስራ አላማ የህክምና ምርመራ ማድረግ ያለባቸውን ሰራተኞች መጠበቅ።
- ሰራተኞች በግድ የ ኤችአይቪ ምርመራ ወይም የእርግዝና ምርመራ እንዳያደርጉ መጠበቅ ወይም ለአሰሪያቸው የ ኤችአይቪ ወይም የእርግዝና ሁኔታቸውን እንዲነግሩ ከመገደድ መጠበቅ።

**አባል ሃገራት ማድረግ ያለባቸው ነገሮች:**

- ቅሬታ ማስገቢያ መንገዶችን መፍጠር እና ለተሰቃዩ፣ በደል ለደረሰባቸው እና መጥፎ ሁኔታ ውስጥ ለነበሩ የቤት ውስጥ ሰራተኞች ጊዜያዊ መጠለያ እና የጤና እንክብካቤ መስጠት።

## 2. የስራ ቅጥር ውል የሚየስገኘው ሙብት ምንድነው?

አንድ አሰሪ ለቤት ሰራተኞች የሚገባው ውል የስራ ሁኔታዎች ግልጽ እና ለመረዳት ቀላል የሆኑ ዝርዝር ጉዳዮችን መያዝ አለበት (አንቀ. 7)።

- የአሰሪው ስም እና አድራሻ እና (ይህ የተለየ አድራሻ ከሆነ) የሚሰሩበት ቦታ፤
- ስራ የመጀመሪያው ቀን እና (ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ከሆነ) የውሉ ጊዜ ገደብ፤
- ምን አይነት ስራ እንደሚሰሩ፤
- ክፍያቸው እና በየስንትጊዜ እንደሚከፈላቸው፤
- መደበኛ የስራ ሰዓት፤
- የቀን እና የሳምንት የእረፍት ጊዜያቸው፤
- በየአመቱ ለምን ያህል ቀናት የውጪ እረፍት እንደሚያገኙ፤
- እነርሱ ወይም አሰሪያቸው እንዴት ውሉን ማቋረጥ እንደሚችሉ፣ የማሳወቂያ ጊዜንም ጨምሮ፤
- የሙከራ ጊዜ (የመታያ)፤
- በሚሰሩበት ቤት ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ አሰሪያቸው የሚሰጣቸው ምግብ እና መኖሪያ ክፍል፤
- በውላቸው መጨረሻ ላይ ወደ ሰራተኛው የመኖሪያ ቤት ወይንም አገር እንዴት እንደሚመለሱ (ወደ መጡበት ሃገር መመለስ)።

አባል ሃገራት ሞዴል ውል አዘጋጅተው ማህበረሰቡ እንዲያገኘው ማድረግ አለባቸው።

በሚቻልበት ሁኔታ ሁሉ፣ አሰሪው ለሰራተኛዋ/ው የጽሁፍ ውል መስጠት አለበት (አንቀ. 7)።

## 3. የቤት ሰራተኞች ሊያገኟቸው የሚገቡ መሰረታዊ የስራ ሁኔታዎች ምንድናቸው?

አንድ አባል ሃገር እርግጠኛ መሆን ያለበት:

- መደበኛ የስራ ሰአታቸው፣ የተጨማሪ የስራ ሰአት ክፍያቸው፣ የቀን እና የሳምንት እረፍት ጊዜ እና አመታዊ ፍቃዳቸው ሃገር ውስጥ ካሉ ሌሎች ሰራተኞች ጋር ተመሳሳይ መሆኑን (አንቀ. 10(1))።
- በእያንዳንዱ ሳምንት ቢያንስ የ 24 ሰአት (አንድ ሙሉ ቀን) እረፍት ማግኘታቸውን (አንቀ. 10(2))።
- በሃገራቸው ዝቅተኛ የክፍያ መጠን ካለ፣ ለቤት ሰራተኞችም መተግበሩን (አንቀ. 11)።
- ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ደምወዛቸውን በካሽ ማግኘታቸውን። የሚስማሙ ከሆነ፣ አሰሪው በቼክ ወይም ወደ ባንክ አካውንታቸው ቀጥታ ማስገባቱን (አንቀ. 12(1))።

አባላ ሃገራትም አሰሪዎች እና ሰራተኞች የስራ ሰአታትን፣ ተጨማሪ የስራ ሰአታትን እና የመጠበቂያ ጊዜዎችን በሚገባ እንዲመዘግቡ ማገዝ አለባቸው።

እንደ የቤት ሰራተኛው የባህል፣ የማህበራዊ እና የሃይማኖታዊ መስፈርት እንጻር ወገኖቹ በሳምንታዊው የእረፍት ቀን ላይ መስማማት አለባቸው።

አሰሪዎች ለሰራተኞች የክፍያ ማረጋገጫ ደረሰኝ ሰጥተው አጠቃላይ መጠኑን ማስረዳት እና ተቀናሽ ካለ ለምን እንደተቀነሰ ማስረዳት።

- በቁሳቁስ የሚከፈላቸው ከሆነ ( ለምሳሌ በልብስ ወይም በምግብ)፡
    - እነዚህ አሰሪው ከሚከፍላቸው ውስጥ የተወሰነው ብቻ መሆኑን፤
    - በእቃ የሚከፈላቸው ዋጋ መጠን ፍትሃዊ እና ተቀባይ መሆኑን፤ እና
    - በእቃ የሚከፈላቸው ክፍያ የሚጠቅማቸው መሆኑን (አንቀ. 12(2))።



**የማህበራዊ ደህንነት ተሳትፎ እና ጥቅማጥቅም በሚሰላበት ጊዜ የሰራተኛው አጠቃላይ ክፍይ (ካሽ ወይም የእቃ) መካተት አለበት።**

**አባል ሃገራት ማድረግ ያለባቸው ነገሮች፡**

- የስራ ቦታዎችን መገምገም የሚችሉባቸውን መንገዶች መፍጠር እና የጤና እና የደህንነት ህጎችን የሚጥሱ አሰሪዎችን መቅጣት።
- በስራ ቦታ ስላለ ደህንነት እና ጤንነት ለቤት ሰራተኞች ምክር እና መረጃ መስጠት።

## 4. የስራ ቦታ ደህንነት እና ጤንነትስ?

- የቤት ሰራተኞች ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጤነኛ የሆነ የስራ ቦታ የማግኘት መብት አላቸው (አንቀ. 13)።
- አሰሪያቸው በስራ ቦታ መጠበቃቸውን ማረጋገጥ አለበት፣ ለምሳሌ፣ እቃዎችን እና መሳሪያዎችን እንዴት በሚገባ እንዲጠቀሙ በማስረዳት እና ለጽዳት የሚሆኑ ዳንቶችን በመስጠት (አንቀ. 13)።



## 5. እና ማህበራዊ ደህንነት?

- የቤት ሰራተኞች ለእርጅና ጊዜ እና ለአካለ ጉዳት ጊዜ የሚሆን ጡረታ የማግኘት መብት አላቸው። ልጅ ለመውለድ በሚሄዱበት ጊዜም የወሊድ ጥቅማ ጥቅሞችን ማግኘት እና ስራቸውን ሲያጡ የስራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞችን እንደ ሌሎች ሰራተኞች የማግኘት መብት አላቸው። (አንቀ. 14(1))።
- መንግስታቸው እንዚህን መብቶች ወዲያውኑ ላይሰጣቸው ይችላል፣ ነገረ ግን በጊዜ ሂደት ውስጥ መስጠት አለበት (አንቀ. 14(2))።

**አባል ሃገራት ማድረግ ያለባቸው ነገሮች፡**

- የማህበራዊ ደህንነት መዋጮ መክፈልን ቀላል ማድረግ፣ ከአንድ በላይ አሰሪ ያላቸውን ሰራተኞች ጭምር።
- ከሌሎች ሃገራት ጋር በመስራትም በሌላ ሃገር ጥቅማ ጥቅም ማግኘት ያለባቸው የቤት ሰራተኞች በሚኖሩበት ሃገር ማግኘት እንዲችሉ ማድረግ።

## 6. ባሰሪዎች ላይ ቅሬታ የማቅረብ መብት አላቸው

አባል ሃገራት ማድረግ ያለባቸው ነገሮች፡

- የቤት ሰራተኞች አሰሪዎቻቸው ላይ በቀላሉ ቅሬታ ማቅረብ እንዲችሉ ወይም መፍታት የሚፈልጉት አለመግባባት ካለ ፍርድ ቤት መሄድ እንዲችሉ (አንቀ. 16)፤ እና
- አሰሪዎቻቸው የስራ ቦታዎችን በማስተካከል ለእነዚህ ህጎች እንዲገዙ ማድረግ (አንቀ. 17)።

- እርዳታ ለሚፈልጉ ሰራተኞችም ሃገራት ብሄራዊ የስልክ ጥሪ መስመሮችን ማዘጋጀት ይችላሉ።
- ለሰራተኞች የፍርድ ቤት ወጪዎች ሃገራት የተወሰነ ገንዘብ ማስቀመጥ ይችላሉ።
- ስደተኛ የቤት ሰራተኞች ወደ ሃገራቸው ከተመለሱ በኋላ ጉዳያቸውን መከታተል ወይም ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ።

**መርማሪዎችም የአሰሪውን ግላዊነት ባከበረ መልኩ የቤት ሰራተኛው የስራ ቦታ በመሄድ መመርመር የሚያስችል ህግ መውጣት አለበት።**

እያንዳንዱ አባል ሃገር እርግጠኛ መሆን ያለበት፡

**ሰራተኞች ከመሄዳቸው በፊት በሚሰሩበት ሃገር ስላሉ መብቶች ማወቅ አለባቸው።**

## 7. ስደተኛ የቤት ሰራተኞችን የሚከተሉትን በማድረግ መጠበቅ፡

- ለስራ ወደ ሌላ ሃገር ከመጓዛቸው በፊት የጽሁፍ ውል ወይም የጽሁፉ የስራ መጠየቂያ መኖሩን (አንቀ. 8(1))፤
- ውሉ ካለቀ በኋላ እንዴት ወደቤታቸው እንደሚመለሱ ውሉ ላይ መጻፉን (አንቀ. 8(4))፤ እና
- የመጡበት ሃገር እና ስራ የሚሰሩበት ሃገር አንድ ላይ በመሆን ሊጠብቋቸው ይገባል (አንቀ. 8(3))።

**የቤት ሰራተኞችም ይህ መብት መቼ እንዳላቸው ግልጽ የሆኑ ህጎች መኖር አለባቸው።**

## 8. የግል የቅጠር ኤጀንሲዎችን ቁጥጥር ያደርጉባቸዋል፡

- የቅጥር ኤጀንሲዎች ሊከተሏቸው የሚችሉት ህጎችን በማዘጋጀት (አንቀ. 15(a))፤
- እነዚህ ኤጀንሲዎች ላይ ያለን የሰራተኞች ቅሬታ መመርመር (አንቀ. 15(b))፤
- ሰራተኞችን በመጥፎ ሁኔታ ከሚያስተናግዱ ኤጀንሲዎች መከላከል (አንቀ. 15(c))፤
- ስደተኛ የቤት ሰራተኞች ስራ እንዲያገኙ የሚረዱ ኤጀንሲዎችን ለመቆጣጠር ከሌሎች ሃገራት ጋር አብሮ መስራት (አንቀ.15(d))፤
- ኤጀንሲዎች ከሰራተኞች ደምወዝ ላይ ምንም ገንዘብ እንደማይቆርጡ እርግጠኛ መሆን (አንቀ. 15(e))።



# ክፍል 2:

## ማጽደቅ ምንድነው ለምንስ አስፈላጊ ሆነ?

ስምምነት 189 ደስ ይላል አይደል? ለቤት ሰራተኞች ጠንካራ መብቶችን ይሰጣል፣ እና በሃገር ደረጃም ምቹ ስራን ያስተዋውቃል። ስምምነቱ የሚለውን ሃገራት እንዲተገብሩት ስምምነት 189 ን ማጽደቅ ምርጥ መንገድ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ፣ ስምምነትን ማጽደቅ ማለት ምን ማለት እንደሆነና አንድ ሃገር ካጸደቀው በኋላ ምን እንደሚፈጠር እናብራራለን። ስምምነቱ ለምን መጽደቅ እንዳለበትም እናብራራለን።

### ስምምነት ማጽደቅ ማለት ምን ማለት ነው?

አንድ አባል ሃገር ስምምነቱን የሚያጸድቀው ህግ አውጪዎቹ (በፓርላመንት ወይም በሴኔት) ስምምነቱ የሚለውን እንደሚያደርጉ ሲያረጋግጡ ነው። ስምምነቱን ያጸደቀ አባል ሃገር ስምምነቱን እውን ለማድረግ ህጎችን፣ ደንቦችን እና መመሪያወችን ማርቀቅ አለበት። ስምምነት 189 ን እውን ማድረግ ላይ፣ አንድ አባል ሃገር ማድረግ ያለበት፡

- ከአሰሪዎች እና ሰራተኞች ድርጅቶች ጋር መማከር፤
- የቤት ስራን ለየት ያለ ባህሪ መረዳት፤ እና
- የቤት ሰራተኞች ከሌሎች ሰራተኞች አንጻር በእኩል ወይም ባላነሰ መልኩ እንክብካቤ ማግኘታቸውን እርግጠኛ መሆን።

ስምምነቱን ባጸደቁ በሁለት አመት ውስጥ፣ አንድ አባል ሃገር ስምምነቱ የሚለውን የትግበራ ሂደት ለ የዓለም ሥራ ድርጅት ሪፖርት ማድረግ አለበት። ከዚያ በኋላ፣ በየአምስት አመቱ ሪፖርት ማድረግ አለበት። የዓለም ሥራ ድርጅት ለአባል ሃገራት በየጊዜው ካጸደቁት ስምምነት ውስጥ ምን ምን እንዳልተገበሩ እና ሃገራዊ ህጎችንም ወደ ስምምነቱ ለማቅረብ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ይነግራል።

ሪፖርት የማድረግ ሂደቱ ላይ የሰራተኛ ድርጅቶች ጠቃሚ ሚና ይጫወታሉ። መንግስት ሪፖርቱን ለዓለም ሥራ ድርጅት ከመላኩ በፊት ለሰራተኛ ድርጅቶች መላክ አለበት። የሰራተኛ ድርጅቶችም ሪፖርቱ ላይ የማይስማሙበት ወይም ክፍተት ካለው አስተያየት ሊሰጡ ይችላሉ። የስራ ድርጅቶች ፌዴሬሽን፣ የራሳቸውን ሪፖርት አዘጋጅተው ለየዓለም ሥራ ድርጅት ሊሰጡ ይችላሉ። የተመዘገበ የቤት ሰራተኛ ህብረትም የራሱን ሪፖርት ለ የዓለም ሥራ ድርጅት በቀጥታ መስጠት ይችላል።

## ስምምነት 189 ለመጽደቅ አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው?

*ስምምነት189 የቤት ሰራተኞችን መብት ይጠብቃል፥*

**1. የመሰብሰብ መብት:** የመሰብሰብ ነጻነት እና የተውጣጣ ድርድር ለ **ስምምነት**189 ዋና ነገሮች ናቸው። አንድ ሃገር **ስምምነት** 189ን አጽድቆ ሲተገብር፣ የሰራተኛ ድርጅቶች የቤት ውስጥ ሰራተኞችን እንዲያግዙ ህጋዊ መሰረት ይሰጣቸዋል (ለምሳሌ፣ ለመሰብሰብ ህጋዊ መብት በመስጠት)።

**2. ከሰራተኛ ድርጅቶች መብቶች ባሻገር:** ስምምነቱ በተጨማሪ መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶችን፣ የቅጥር ኤጀንሲዎች ቁጥጥርን እና ለስደተኛ የቤት ውስጥ ሰራተኞች እኩል እንክብካቤን ይሸፍናል።

**3. ስደተኛ የቤት ውስጥ ሰራተኞችን መጠበቅ:** ስምምነት189ን ማጽደቅ ላኪ ሃገራት ውጪ ያሉ የሰራተኞቻቸውን መብት እንዲጠብቁ ያደርጋል። እንደውም፣ የተለያዩ ሃገራት ያላቸውን የስራ ህጎች በማቀራረብ ላኪ እና ተቀባይ ሃገራት የስደተኛ የቤት ውስጥ ሰራተኛ መብቶች እንዲጠበቁ አንድ ላይ እንዲሰሩ ያደርጋል።

**4. ማካተት:** በብዙ ሃገራት የቤት ውስጥ ሰራተኞች በህጉ ጥበቃ አይደረግላቸውም፣ ብቻቸውንም ስላሉ ብዝበዛ እና በደል ይደርስባቸዋል። ስምምነት189 ለቤት ውስጥ ሰራተኞች የህግ ጥበቃ የመስጠት አላማ አለው።

**5. መብቶችን ማስጠበቅ:** መንግስታት ይቀያየራሉ፣ ብዙ ጊዜም ህጎች አብረው ይቀየራሉ። ነገር ግን መንግስት ቢቀየርም እንኳን፣ ስምምነቶች ያጸደቋቸውን ሃገራት አንድ ላይ ይይዛሉ። ስምምነት189 ን ማጽደቅ አዲስ መንግስት ለቤት ሰራተኞች መስፈርቱን እንዳያወርደው ይከላከላል።

**6. ተጠያቂነትን ማሻሻል:** የስራ ድርጅቶች ስምምነት189 ን በመጠቀም በደሎችን እና ብዝበዛዎችን ማውገዝ ይችላሉ እና የሃገሪቱን ሂደት ለማወቅ የ የዓለም ሰራተኛ ድርጅትን ስርአት መጠቀም ይችላሉ።

# ክፍል 3:

# ስምምነት189 ለቤት ሰራተኞች እንዴት እውን መሆን ይችላል?

ስምምነት189 ን ማጽደቅ ለምን እንደሚጠቅም አውርተናል። በዚህ ክፈል ውስጥ፣ የስምምነቱ ክፍሎች በስራ ቦታ ለቤት ሰራተኞች እንዴት እውን እንደሚሆኑ እንመለከታለን። የሚከተሉትን ሶስት ደረጃዎች እንሰመለከታለን፡

**ደረጃ 1:** ሃገርዎ ስምምነት189 ን ማጽደቁን ይወቁ

**ደረጃ 2:** የማረጋገጫው ዝርዝር በመጠቀም ህጋችሁ ላይ ያለውን ክፍተት ይፈልጉ።

**ደረጃ 3:** ስምምነት189 ን በመጠቀም የቤት ሰራተኞች ስምምነት189 እንደሚያስፈልጋቸው ጠቅላላ ግንዛቤ አስጨብጡ።

## ደረጃ 1: ሃገርዎ ስምምነት189ን ማጽደቁን ይወቁ

በኦገስት 2018፣ 25 የሚሆኑ ሃገሮች ስምምነት189 ን አጽድቀዋል፣ እና የፔሩ ኮንግረስም ለማጽደቅ ተስማምቷል። እነዚህ 25 ሃገራትም ከማህበራዊ አጋሮች ጋር በመሆን፣ እርስዎንም በመጨመር ስምምነቱን ስራ ላይ ለማዋል ህጎችን፣ ደንቦችን እና ስምምነቶችን ያረቃሉ።

ሃገርዎ ስምምነት189 አጽድቆ ከሆነ፣ እውን እንዲሆን ቅስቀሳ ማድረግ የቻላሉ ማለት ነው። የ የዓለም ሥራ ድርጅት ስርአት እንዳለ እና የእርስዎ ሃገር ለ ለዓለም ሥራ ድርጅት ሪፖርት ማድረግ እንዳለበት ያስታውሱ።

ሃገርዎን በሰንጠረዥ 1 ላይ የሚያገኙት ከሆነ ይመልከቱ።

**ሰንጠረዥ 1: በኤፕሪል 2018 C189 ን ያጸደቁ ሃገሮች**

| | |
|---|---|
| አፍሪካ | ሰሜን አሜሪካ |
| ጊኒ | ኮስታሪካ |
| ማውሪሺየስ | ዶሚኒካን ሪፐብሊክ |
| ደቡብ አፍሪካ | ጃማይካ |
| እስያ | ኒካራጉዋ |
| ፊሊፒንስ | ፓናማ |
| አውሮፓ | ደቡብ አሜሪካ |
| ቤልጂየም | አርጀንቲና |
| ፊንላንድ | ብራዚል |
| ጀርመን | ቦሊቪያ |
| አየርላንድ | ቺሊ |
| ጣሊያን | ኮሎምቢያ |
| ፖርቹጋል | ኢኳዶር |
| ስዊዘርላንድ | ጉያና |
| | ፓራጓይ |
| | ኡራጋይ |




ስምምነቱን ያጸደቁት ሃገሮች የዘመነ ዝርዝር ለማግኘት፣ እዚህ ጋር ይሂዱ፡ ***https://www.ilo.org/dyn/normlex/en/f?p=NORMLEXPUB:11300:0::NO::P11300_INSTRUMENT_ID:2551460***

*ሃገርዎ ከላይ ባለው ዝርዝር ውስጥ ከሌለ፣* ስምምነቱን ስላላጸደቀ ሊሆን ይችላል እና ከታች ያለውን ሰንጠረዥ 2 ይመልከቱ። ሰንጠረዥ 2 የሚያሳየው ስምምነቱን ያላጸደቁ ነገር ግን ለቤት ሰራተኞችን ጥበቃ የሚያደርጉበት ህግ ያላቸው ሃገሮች ዝርዝር ነው። ከእነዚህ ውስጠ አንዳንድ ሃገሮች ምንም እንኳን ስምምነቱን ባያጸድቁም ከ ስምምነት189 ጋር የሚጣጣም ህጎችን ቀርጸዋል።

ሃገርዎ እንደዚህ ከሆነ ከታች ያለውን ሰንጠረዥ 2 ይመልከቱ።

**ሰንጠረዥ 2: ሰንጠረዡ ስምምነት189 ን ከተቀበሉ በኋላ ህጋቸውን ወይም ፖሊሲያቸውን የቤት ሰራተኞችን ለመጠበቅ ሲሉ ያስተካከሉ ሃገሮችን ያሳያል።**

| አፍሪካ | እስያ |
|---|---|
| ኬፕ ቬርዴ | ባህሬን |
| ኬንያ | ባንግላዲሽ |
| ላይቤሪያ | ህንድ |
| ማውሪታኒያ | ጆርዳን |
| ሞሮኮ | ኩዌት |
| ናሚቢያ | ኔፓል |
| ታንዛኒያ | ፓኪስታን |
| ኡጋንዳ | ሳውዲ አረቢያ |
| ዛምቢያ | ሲንጋፖር |
| **አውሮፓ** | ታይላንድ |
| ስፔን | ቬትናም |
| **ሰሜን አሜሪካ** | **ደቡብ አሜሪካ** |
| ኤል ሳቫዶር | ቬንዙዌላ |
| አሜሪካ | |




## ደረጃ 2፡ የማረጋገጫ ዝርዝሩን በመጠቀም በሃገርዎ ያሉትን ክፍተቶች ይፈልጉ

አሁን ሃገርዎ ያለበትን ሁኔታ ካወቅ፣ ሰንጠረዥ 3 ላይ ያለውን የማረጋገጫ ዝርዝር በመጠቀም ሃገርዎ ስምምነት189 ን እንዳጸደቀው ወይም እንዳላጸደቀው ይወቁ።

- **ሃገርዎ ስምምነት189 ን ካላጸደቀው፣ የሚጠቀሙት፡**
  - በ ስምምነት189 ላይ የክፍተት መጠን ጥናት ለማካሄድ፡ ከስራ ህጋችው ውስጥ የትኞቹ ከ ስምምነት189 ጋር የተጣጣሙ ናቸው፣ እና የትኞቹስ አይገናኙም?
  - የመንግስት ባለስልጣናት እና ህግ አውጪዎች ስለ ስምምነት189 ወይም ምን እንደሚል አያውቁም። ይህን የማረጋገጫ ዝርዝር ሃገርዎ ውስጥ የግንዛቤ ክፍተት ካለ ለማወቅ ይጠቀሙበት።
  - በሃገረዎ ህግ እና በ ስምምነት189 መካከል ክፍተት እንዳለ ለቤት ሰራተኞች ማስተማሪያ ነው። ይህ የድርጅቱን አባላት በማስታጠቅ ድርጅቱን ወደ ተሻለ ደረጃ ያሳድገዋል።
- **ሃገርዎ ስምምነት189 ን ካጸደቀ፣ የሚጠቀሙት:**
  - የመንግስት ባለስልጣናትን ስለ ስምምነት189 ለማሳወቅ እና መንግስት ለቤት ውስጥ ሰራተኞች ጥበቃ  እንዲያደርግ ውስጡ ያለውን ነገር እንዲያውቅ፤
  - ለመንግስት ሪፖርቶች አስተያየት መስጠት ወይም መረጃን ለ ለዓለም ሥራ ድርጅት መላክ፤ እና
  - በሃገረዎ ህግ እና በ ስምምነት189 መካከል ክፍተት እንዳለ ለቤት ሰራተኞች ማስተማሪያ ነው። ይህ የድርጅቱን አባላት በማሳወቅ ድርጅቱን ወደ ተሻለ ደረጃ ያሳድገዋል።

ሰንጠረዥ 3፡ ስምምነት189 የማረጋገጫ ዝርዝር

| | አዎ | አይደለም | አስተያየቶች |
|---|---|---|---|
| **ሀ) የቤት ሰራተኞችን መሰረታዊ መብቶች ለመጠበቅ እርምጃዎች (ህጎች፣ ፖሊሲዎች፣ ልምዶች) አሉ?** | | | |
| • አሰሪዎች የቤት ሰራተኞችን ፍትሃዊ በመሆነ መልክ እንዲንከባከቡ እና ምቹ የስራ ሁኔታ እንዲኖራቸው የሚጠይቅ (አንቀ. 6)። | | | |
| • የቤት ሰራተኞች አንድ ድርጅትን ሲመሰርቱ ወይም ሲቀላቀሉ እና/ወይም ከአሰሪዎቻቸው ጋር ሲደራደሩ ጥበቃ የሚየደርግላቸው (አንቀ. 3(2)(a)፣ (አንቀ. 3(3))። | | | |
| • ልጆች ትምህርታቸውን ሳይጨርሱ የቤት ስራዎችን እንዳይሰሩ ጥበቃ የሚያደርግ (አንቀ. 3(2)(c)፣ (አንቀ. (4))። | | | |
| • ሰዎችን የቤት ሰራተኛ እንዲሆኑ እንዳይገደዱ ጥበቃ የሚያደርግ (አንቀ. 3(2)(b))። | | | |
| • የቤት ሰራተኞች በስራ ቦታ መድልዎ እንዳይደርስባቸው ጥበቃ የሚያደርግ (አንቀ. 3(2)(d))። | | | |
| • የቤት ሰራተኞችን ከበደል፣ ከትንኮሳ እና ከሁከት ጥበቃ የሚያደርግ (አንቀ. 5)። | | | |
| • ሰራተኞች  በሚሰሩበት ቤት ወይም ሌላ ቦታ መኖርን መምረጥ እንዲችሉ ጥበቃ የሚያደርግ (አንቀ. 9(a))። | | | |
| • የቤት ሰራተኞችን በግላዊነት፣ በተጠባባቂ ሰአታቸው እና በእረፍት ቀናቸው ከቤት መውጣት ላይ ጥበቃ የሚያደርግ (አንቀ. 6፣ 9(b) እና 10(3))። | | | |
| • ሰራተኞች የማንነት መገለጫ ሰነዶቻቸውን ራሳቸው ጋር እንዲቆይ ጥበቃ የሚያደርግ (አንቀ. 9(c))። | | | |

| | አዎ | አይደለም | አስተያየቶች |
|---|---|---|---|
| **ለ) ህጋችሁ ሰራተኞች የስራ ቅጥር ውል እንዲኖራቸው ያረጋግጣል?** | | | |
| • አሰሪዎች የቤት ውስጥ ሰራተኞችን የውል ዝርዝር እንዲያብራሩ እና በሚቻልበት ጊዜ የጽሁፍ የውል እንዲሰጥ ይጠይቃል?<br><br>ውሉ የሚከተሉትን ነገሮች መሸፈን አለበት፣ ለምሳሌ፣ የውሉ ጊዜ ገደብ፣ የስራው አይነት፣ ክፍያዎች፣ የስራ ሰአታት፣ የእረፍት ጊዜያት እና እረፍት (አንቀ. 7)። | | | |
| **ሐ) ህጋችሁ የቤት ሰራተኞችን መሰረታዊ የስራ ሁኔታዎች ያጠቃልላል?** | | | |
| • መደበኛ የስራ ሰአታቸው፣ የተጨማሪ ሰአት ስራ ክፍያቸው፣ እረፍት ጊዜ እና አመታዊ ፍቃዳቸው እንደ ሌሎች ሰራተኞች ተመሳሳይ መሆኑን (አንቀ. 10(1))። | | | |
| • ብሄራዊ መነሻ ክፍያ (ካለ) ለቤት ሰራተኞች መተግበር (አንቀ. 11)። | | | |
| • ሰራተኞችን ቢያንስ በሳምንት የ 24 ሰአት እረፍት ማረጋገጥ (አንቀ. 10(2))። | | | |
| • ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ክፍያ በካሽ ወይም (የሚስማሙ ከሆነ) በቼክ ወይም ወደ ባንክ አካውንታቸው ቀጥታ መግባቱን ማረጋገጥ (አንቀ. 12(1))። | | | |
| • ከክፍያቸው ውስጥ የተወሰነውን ብቻ በአይነት የሚቀበሉ ሰራተኞችን ጥበቃ ማድረግ (አንቀ. 12(2))። | | | |
| **መ) የቤት ሰራተኞችን ደህንነት እና ጤንነት በስራ ቦታ የሚጠብቁ እርምጃዎች አሉ (አንቀ. 13)?** | | | |
| **ሠ) የቤት ውስጥ ሰራተኞችን በማህበራዊ ደህንነት ጥቅማ ጥቅሞች (ለምሳሌ፣ ጡረታ፣ ወሊድ እና የአካል ጉዳት ጥቅማ ጥቅሞች) ውስጥ የማካተት እርምጃዎች አሉ (አንቀ. 14)?** | | | |

| | አዎ | አይደለም | አስተያየቶች |
|---|---|---|---|
| **ረ) የቤት ሰራተኞች አሰሪዎች ላይ ቅሬታ የማስገባት መብት አላቸው?** | | | |
| • የቤት ውስጥ ሰራተኞች አሰሪያቸው ላይ ቅሬታ ማቅረብ ወይም መፍታት የሚፈልጉት አለመግባባት ካለ ፍርድ ቤት በቀላሉ መሄድ ይችላሉ (አንቀ. 17(1))? | | | |
| • የስራ ተቆጣጣሪዎች የግል ቤቶችን አሰሪዎች በህጉ መሰረት እያሰሩ መሆኑን ይቆጣጠራሉ (አንቀ. 17(1))? | | | |
| **ሰ) ሃገራችሁ ለስደተኛ የቤት ውስጥ ሰራተኞች ጥበቃ ያደርጋል?** | | | |
| • ስደተኛ ሰራተኞች ከሃገራቸው ሳይወጡ በፊት የቅጥር ውል እንዲኖራቸው ያስፈልጋል (አንቀ. 8(1))? | | | |
| • መንግስታችሁ የቤት ውስጥ ሰራተኞችን ለመጠበቅ ከሌሎች ሃገራት ጋር አብሮ መስራት አለበት (አንቀ. 8(4))? | | | |
| **ሸ) ህጋችሁ የቤት ውስጥ ሰራተኛን የሚያስቀጥሩ የቅጥር ኤጀንሲዎችን ይቆጣጠራል?** | | | |
| • የቅጥር ኤጀንሲዎች የሚከተሉት ህጎችን መንግስት ማርቀቅ አለበት (አንቀ.15(a))? | | | |
| • የቅጥር ኤጀንሲዎች ላይ የሚመጡ ቅሬታዎችን መንግስት መመርመር አለበት (አንቀ. 15(b))? | | | |
| • ሰራተኞችን በመጥፎ ሁኔታ ከሚያስተናግዱ ኤጀንሲዎች ይጠብቃል (አንቀ. 15(c))? | | | |
| • ኤጀንሲዎችን መቆጣጠር አስፈላጊ ሲሆን መንግስታት ከሌላ ሃገሮች ጋር መስራት አለባቸው (አንቀ. 15(d))? | | | |
| • ኤጀንሲዎች ከቤት ውስጥ ሰራተኞች ክፍያ እንዳይቀንሱ ይከለከላሉ (አንቀ. 15(e))? | | | |

# ደረጃ 3፡ ስምምነት 189 ን የቤት ሰራተኞች ስለ ስምምነት189 አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይጠቀሙበት

በዚህ ክፍል ውስጥ፣ ለቤት ውስጥ ሰራተኞች የተሻለ መብቶች እና የስራ ሁኔታዎችን ማሸነፍ የምንችላባቸውን ስልቶች እንመለከታለን። ሃገሮች ከ ስምምነት189 አንጻር ህጎቻቸውን እና ልምምዶቻቸውን እንዴት እንዳስተካከሉ ምሳሌዎችንና በዚህ ሂደት ውስጥ የሰራተኛ ድርጅቶች የተጫወቱትን ሚና እንመለከታለን። ስምምነት189 ን ባጸደቁ ሃገሮች ያሉ ድርጅቶች የሚጠቀሙትን ስልት እና ስምምነት 189 ን ባላጸደቁ ሃገራት ያሉ ድርጅቶች አሰራሮችን እንመለከታለን። ሃገራቸው ስምምነት 189ን ተቀበለ ወይም አልተቀበለ ሁሉም የሰራተኛ ድርጅቶች መከተል ያለባቸውን ስልቶች በተጨማሪ እንመለከታለን።

## ሃገርዎ ስምምነት189ን ካጸደቀ

በዚህ ትልቅ ድል እንኳን ደስ አልዎት! ያስታውሱ፣ ስራው ገና አላለቀም እና ትግሉ ይቀጥላል። የሞሉትን ሰንጠረዥ 3 በመጠቀም፣ አሁን ካለው ህግ ውስጥ የትኛው ስምምነት አንደጎደለ ይለዩ፡ ይህ ድርጅትዎ ውስጥ ያሉ ሁሉም የቤት ውስጥ ሰራተኞች ሁሉ ስለ ስምምነት 189 እውቀት እንዲኖራቸው እና የአካባቢ ህግዎ ምን እንደሚል ለማወቅ ጠቃሚ ነው።

ከዚህ በታች ሌሎች የቤት ሰራተኛ ድርጅቶች በስምምነት189 መሰረት መብቶችን እንዴት እንዳስከበሩ እናያለን፡

1. **መንግስትን ቅስቀሳ ማድረግ** ይህም በስምምነት189 ውስጥ ያሉትን መብቶች እና ጥበቃዎች ለሰራተኞች እንዲሰጥ አንዳንድ የቤት ሰራተኞች ከቤት ሰራተኛ ህግ ጋር ተያይዞ ያለው ሙሉ ህግ አንዲለወጥ ጠይቃዋል። በሌላ ጉዳዮች፣ በአንድ ወይም በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የሰራተኛ ድርጅቶች በመሳተፍ የቤት ውስጥ ሰራተኞች መብቶች እንዲጠበቅ እና ህጉ የቤት ውስጥ ሰራተኞችን መብት እንዳያሳንስ ለውጥ እንዲኖር ብዙ ድርጅቶች ተሳትፈዋል።

**ለምሳሌ፡**

የጊኒ የቤት ሰራተኞች ህብረት Syndicat National des Employés de Maison de Guinée (SYNEM-GUINEE) እና ብሄራዊ ፌዴሬሽኑ ቀድሞ ለቤት ውስጥ ሰራተኞች አነስተኛ ጥበቃ የሚያደርግ የነበረውን የስራ ህግ አንድ ላይ በመሆን እንዲከለስ በተደረገው ሂደት ላይ ተሳትፈዋል። አዲሱ የስራ ህግ ጊኒ ስምምነት189 ን በ 2017 ከማጽደቋ በፊት ስራ ላይ የዋለና ለቤት ውስጥ ሰራተኞች የበለጠ መብቶችን የሚሰጥ ነው። በ 2018፣ ህብረቱ እና ፌዴሬሽኑ የቤት ሰራተኞችን ወደ ስምምነት189 ለማስጠጋት ብሄራዊ ህግ ቀርጸዋል። ረቂቅ ህጉ በሞሮኮ የቤት ሰራተኛ ህግ ላይ የተመረኮዘ ሲሆን፣ የስራ ሰአታትን፣ አመታዊ ፍቃድን፣ የቤተሰብ እረፍት፣ የስራ ቅጥር ኤጀንሲዎችን እና የልጆች ስራን በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ቁጥጥር የደርጋል። ህብረቱ እና ፌዴሬሽኑ ረቂቅ ህጉን ለብሄራዊ ስብሰቡ ለማቅረብ እቅድ ይዘዋል።

**2 የቤት ውስጥ ሰራተኞችን አስከፊ ሁኔታ በተመለከተ ሰራተኞችን በማሰባሰብ** መንግስት የቤት ሰራተኞችን ጉዳይ ቅድሚያ የሚሰጠው ትኩረቱ እንዲሆን እና የህዝቡን እና የአሰሪውን እገዛ እንዲፈልግ ማድረግ።

**3. በ አለም ስራ ድርጅት ሪፖርት ማድረግ ሂደት ውስጥ መሳተፍ፣** ወይ መንግስት ያቀረበውን ሪፖርት አስተያየት መስጠት ወይም ህብረቱ የሚያስገባ ው ሪፖርት ላይ አስተዋእጾ ማድረግ፣ ወይም የተመዘገበ ህብረት ከሆነ የራስን ሪፖርት ማዘጋጀት። እገዛቸውን ለማግኘት በ አለም ስራ ድርጅት ድጋፍ የሚወከሉ ከህብረት ፌዴሬሽኖች ጋር አብሮ መስራት።

**4. ስምምነቱን ማስፈጸም ላይ ዓለም ስራ ድርጅት የመንግስት ሪፖርት ላይ የተሰጠውን አስተያየት ማግኘት።** መንግስት የራሱን ስምምነት189 ሪፖርት ካስገባ በኋላ፣ የ ዓለም ሥራ ድርጅት ባለሙያዎች ኮሚቴ መንግስት በምን ጉዳዮች ዙሪያ ማሻሻል እነዳለበት ይጽፋሉ። አንዳንድ ጉዳዮችንም መንግስት በምን መልኩ እየፈታ እነደሆነ ለመንግስት ጥያቄን ያቀርባሉ። የባለሙያዎች ኮሚቴ አስተያየቶች ትልቅ ክብደት ያለው ስለሆነ፣ መንግስትን ተጠያቂ ለማድረግ ለህብረቶች ትልቅ መሳሪያ ነው።

**5. መንግስት የተቀመጡትን ሁሉንም የ ስምምነት189 መስፈርቶችን ምንም እያሟላ እንዳልሆነ ለ ለዓለም ሥራ ድርጅት ማብራራት። የዓለም ሥራ ድርጅት** መንግስትን የቀረበውን ጥያቄ እንዲመልስ ይጠይቀዋል። መንግስት ምላሽ የማይሰጥ ከሆነ ወይም የሚያረካ መልስ ከሌለው፣ ዓለም ሥራ ድርጅት የቀረበውን ጥያቄ እና መልሱን ሊያትም ይችላል።

**6. ስለ የመሰብሰብ መብት፣ የመሰብሰብ ነጻነት እና የተውጣጣ ድርድር ቅሬታዎችን ማሰማት።** እነዚህ ቅሬታዎች በስምምነት ቁ. 87 ስር በመሰብሰብ መብት እና በመሰብሰብ ነጻነት እና ስምምነት ቁ. 98 ደግሞ በመሰብሰብ ነጻነት እና የተውጣጣ ድርድር ስር ይሸፈናሉ። በመሰብሰብ ነጻነት ላይ ያለው የዓለም ሥራ ድርጅት ኮሚቴ ቅሬታዎቹን በማስተናገድ እንዴት እነዚህን ችግሮች መፍታት እነደሚቻል ሪፖርት እና ማጠቃለያ ያዘጋጃል።

## ሃገርዎ ስምምነቱን ካላጸደቀ

ተስፋ አለ! ሃገርዎ ስምምነቱን ካላጸደቀማድረግ የሚችሏቸው ጠቃሚ ነገሮች እዚህ ጋር ተገልጸዋል እንዲሁም አንዳንድ ሃገሮች ያደረጉትም በምሳሌነት ተገልጿል።

**1. መንግስት ለምን ስምምነቱን እንዳላጸደቀ ማወቅ**

i) አንድአንድ ሃገሮች ስምምነቱን የሚያጸድቁት ብሄራዊ ህጋቸውን ከስምምነቱ ጋር ካመሳሰሉ በኋላ ነው። ለዓለም ሥራ ድርጅት እነዚህን አባል ሃገራት ለምን እንዳላጸደቁ ሪፖርት እንዲያደርጉ ሊጠይቅ ይችላል። እነዚህ ሃሮች ስምምነት189ን በኋላ በራሳቸው ሂደት ውስጥ ሊያጸድቁት ይችላሉ።

**ለምሳሌ፡**

የኡጋንዳ መንግስት ስምምነት189 ን ለማጽደቅ ቃል ገብቷል። መንግስቱም ከማጽደቁ በፊት ህጎቹን ከስምምነቱ ጋር ለማመሳሰል ወስኗል። የስራ ሚኒስተርም ለቤት ሰራተኞች ጥበቃ የማየደርገውን የስራ ጤንነት እና ደህንነት ህጉን እየገመገመ ነው። የቤት ሰራተኞችን የሚያካትት የመነሻ ክፍያ ህግን እያረቀቀ ነው። መንግስትም በዚህ ውስጥ የሌሉትን የሰራተኞች ብሄራዊ ደህንነትን ለመስጠት የብሄራዊ ማህበራዊ ደህንነት ፈንድ ህግን ለመቀየር መንገድ ላይ ነው። የኡጋንዳ ሆቴሎች፣ ምግብ፣ ቱሪዝም፣ ሱፐርማርኬቶች እና የተባበሩ ሰራተኞች ህብረት (UFTAWU) በሂደቱ ላይ በመሳተፍ የተከለሱት ህጎች ለቤት ሰራተኞች ጥበቃ እንዲያደርጉ እየጠየቁ ነው።

ii) ሃገሮች ስምምነቶችን ላለማጸደቅ ሊወስኑ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከስምምነቱ ጋር የሚስማሙ ህጎችን ሊያረቁ ይችላሉ። በእነዚህ ሃገሮች፣ ህጎችን እና ፖሊሲዎችን ለመቅረጽ ስምምነቱ እንደ መመሪያ ሊያገለግል ይችላል።

**ለምሳሌ፡**

የዙምባብዌ መንግስት ስምምነት189 ን በዚህ ሰአት ላለማጽደቅ የወሰነ ቢሆንም፣ የቤት ሰራተኞች ቅጥር ደንብን በ ስምምነት 189 መሰረት ለመቀየር ቃል ገብቷል። የዙምባብዌ የተባበሩት የሰራተኞች ህብረት ከ ስራ ሚኒስቴር ጋር በመሆን ስደተኛ የቤት ሰራተኞች ስራን ለመቆጣጠር እና ብሄራዊ ደህንነት ለመስጠት እና ቤት ውስጥ እየኖሩ ለሚሰሩ የቤት ሰራተኞች ጥበቃ ለማድረግ አብረው እየሰሩ ነው። ህብረቱ እና መንግስት ደንቦቹ ከተከለሱ በኋላ ሁሉም ተገዢ መሆኑን ለመቆጣጠር ተስማምተዋል። መንግስት ከዚህ በኋላም ማጽደቅ ላይ ያለውን ሃሳብ እንደገና ያየዋል።

iii) አንዳንድ  ሃገሮች የማያጸድቁት ከስምምነቱ መፈጸም ጋር ተያይዞ ያለውን ጫና እና ክፍያ ላይ ስጋት ስላላቸው ነው።

2. የቤት ሰራተኞችን የሚመለከቱ **አሁን ስራ ላይ ያሉ ህጎች መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ ቅስቀሳ ማድረግ** ፣ ለምሳሌ፣ አሰሪዎች ለህጉ ተገዢ በቀላሉ እንዲሆኑ ማድረግ ወይም ለምርመራዎች ገንዘብ መበጀት።

**ለምሳሌ፡**

በ 2013፣ የ ፔሩ እንባ ጠባቂ መንግስት የቤት ሰራተኞችን ለመጠበቅ እያስፈጸመ ስላለው ህግ ሪፖርት አውጥቶ ነበር። ሪፖርቱ የገለጸው በጣም ትንሽ የሆኑ የቤት ሰራተኞች ብቻ ለምን ለብሄራዊ ጥበቃ እንደተመዘገቡ ነው። ከእነዚህ ውስጥ የግንኙነት እና ግንዛቤ ማነስ ፣ ከባድ የሆነ የምዝገባ መስፈርት እና ምቹ ያልሆኑ ሂደቶች ናቸው። አንዳንድ የመንግስት ኤጀንሲዎች እና የአካባቢ ባለስልጣናት የሰራተኞችን ግንዛቤ በመጨመር እና አሰሪዎች ሰራተኞችን መመዝገብን ቀላል በማድረግ ምላሽ ሰጥተዋል። በ 2016፣ የቤት ሰራተኛ ድርጅቶች መንግስት የእንባ ጠባቂ ቢሮ ምክሮችን ተግባራዊ እንዲያደርግ ቅስቀሳ አድርገዋል።

## ለሁሉም የሰራተኛ ድርጅቶች የሚሆኑ ስልቶች

የእርስዎ መንግስት ስምምነቱን አጸደቀውም አላጸደቀውም፣ የእርስዎ የሰራተኛ ድርጅት ከተለያዩ አካላት ጋር በመሆን ግንኙነቶችን/ትብብሮችን ማቀናጀት እና መገንባት ይችላል። አንዳንድ ምሳሌዎች ከዚህ በታች ተገልጸዋል፡

1. **ከሚዲያው ጋር በመስራት** ስለ የቤት ሰራተኞች አስተዋጽኦ እና ስለ እነርሱ ያለውን አመለካከት ስለመቀየር ጠቅላላ ግንዛቤን ማስፋፋት። በተለያዩ ሃገሮች ያሉ ድርጅቶች ጋዜጠኞችን፣ ቲቪ እና ሬዲዮ ፕሮግራሞችን፣ ቲያትር፣ ሙዚቃ፣ ፊልሞችን እና ማህበራዊ ድረገጾችን በቅስቀሳዎቻቸው ተጠቅመዋል።

2. የሚመለከታቸውን ጉዳዮች መፍትሄ ለመስጠት**ሰራተኞችን ማሰባሰብ፣ መደገፍ እና ማስታጠቅ** ፡ ሰራተኞችን ስለመብታቸው ማስተማር፣ የክህሎት ስልጠና መስጠት፣ የድርድር ስልጠና መስጠት እና የቅጥር እገዛ ማድረግ ለምሳሌ ሞዴል የቅጥር ውሎችን። ይህ ለቤት ውስጥ ሰራተኞች ስምምነት 189ን እውን ማድረግ ላይ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

**ለምሳሌ፥**

በ 2013፣ የአለም አቀፍ የቤት ሰራተኞች ኔትወርክ (IDWN) እና የ ታንዛኒያ CHODAWU፣ በሚኖሩበት ቤት ውስጥ የሚሰሩ የቤት ሰራተኞችን ስለ ህጋዊ መብቶቻቸው፣ የእረፍት ጊዜ እና ፍቃዶችን በተመለከተ ስልጠና ሰጥተዋል። የጊዜ መመዝገቢያ በመጠቀም እንዴት የስራ ሰአታቸው እና ክፍያቸውን ማስላት እንደሚችሉ ተምረዋል።

3. የቤት ሰራተኞችን በተመለከተ የአሰሪዎች ሃላፊነት ምን እንደሆነ እና የቤት ውስጥ ሰራተኞችን መብቶች ማክበር እንዲችሉ እንዲሁም ለስምምነቱ ተገዢ እንዲሆኑ ሰልጥነዋል።

**ምሳሌዎች፥**

የ የዐለም አቀፍ የቤት ሠራተኛ ፌደሬሽን/ የዓለም ሰራተኛ ድርጅት (IDWF/ILO)ፍትሃዊያ ቤት የሚለው ቅስቀሳ አሰሪዎች ለቤት ሰራተኞች የተሻለ የስራ እና የኑሮ ሁኔታዎችን እንዲያመቻቹ ቃል እንዲገቡ የሚጠራ ነው፡፡ ሰራተኞችን ቢያንስ ዝቅተኛ ክፍያ እንዲያገኙ ማድረግ፣ ተቀባይነት ያላቸው የስራ ሰአታትን እና እረፍት ጊዜ መስጠት፣ በጽሁፍ የቅጥር ውል መዋዋል፣ የጤና እንክብካቤ እንዲያገኙ እና ከበደል እና ከትንኮሳ ነጻ እንዲሆኑ ማድረግን ያጠቃልላል።

**(የበለጠ ለመማር፣ የሚከተለውን ይጎብኙ: idwfed.org/myfairhome)**

---

የጊኒ የቤት ሰራተኞች ህብረት (SYNEM GUINEE) በ 2011 ከተመሰረተ ጀምሮ፣ C189 ለመተግበር ከአሰሪዎች ፌደሬሽን ጋር በመተባበር እየሰራ ነው። ጊኒ ለቤት ሰራተኞች የአሰሪዎች ማህበር የላትም፡፡ ነገር ግን ትልቁ የአሰሪዎች ፌዴሬሽን በመስኩ ውስጥ ያሉትን አሰሪዎችን ይወክላል።
SYNEM አሰሪዎችን ግንዛቤ የመስጠት ቅስቀሳዎች ላይ የሚያተኩር ሲሆን ፌዴሬሽኑን ወደ ስልጠና ወርክሾፖች ይጋብዛል።

4. **አንዳንድ አስተባባሪዎችን/አስተማሪዎችን በድርጅቱ ውስጥ ህጉን እንዲያውቁ (ፓራሊጋል እንዲሆኑ) ማሰልጠን።** ፓራሊጋሎች ለሰራተኞች የቀን ተቀን ትግሎቻቸው ላይ እገዛ መስጠት ይችላሉ እና መንግስት የተወሰኑ ህጎችን እንዲያስፈጽም የሰራተኞች ድርጅቶች በሚያደርጉት ጥረቶች መሪዎችን ያግዛሉ።

5. ለቤት ሰራተኞች ጥበቃ የሚያደርጉ **አሁን ስራ ላይ ያሉ ህጎች እና ፖሊሲዎች ሙሉ በሙሉ እንዲተገበሩ ለመንግስት ቅስቀሳ ማድረግ፣** ለምሳሌ፣ አሰሪዎች የጡረታ ገንዘብ የሚከፍሉበትን መንገድ ቀላል ማድረግ።

6. **በህግ ማሻሻል ላይ ተሳታፊ የሆኑ ተቋማት ጋር ግንኙነቶችን መገንባት** ይህም የቤት ሰራተኞች ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ነገሮች ካሉ ቶሎ ማወቅ እንዲቻል ነው (ለምሳሌ፣ በስራ ጉዳዮች ላይ የፓርላመንት ኮሚቴ እና የህግ ማሻሻል ኮሚሽን)።

7. በ ዓለም ሥራ ድርጅት  የተወከሉ እና በ ዓለም ሥራ ድርጅት  ስምምነቶች በተመለከተ ተጠሪ ከሆኑ **ከብሄራዊ ህብረት ፌዴሬሽኖች ጋር መስራት።**
የቤት ሰራተኞች ድርጅቶች ማስፈጸምን እና ትግበራን በተመለከተ ፌደሬሽኑን ማማከር ይችላሉ።

**ለምሳሌ፡**

*"በላይቤሪያ ውስጥ ያለነው የቤት ሰራተኞች ህብረት፣ ገና ጀማሪ ህብረት እንደመሆናችን፣ ከዋናው እናት አካል ጋር መገናኘት አለብን ... ምክንያቱም ህጻን ልጅ ብድግ ብሎ ከመንግስት ጋር መታገል ስለማይችል ነው። ማንም የሚያውቅህ የለም... ስለዚህ፣ ከላይቤሪያ ሠራተኛ ኮንግረስ ጋር በጋራ መስራት ጀምረን ያለብንን ችግሮች አማከርናቸው። እነርሱ ተናጋሪ አካል ናቸው እና እኛ ም ከነሱ ጋር ጋር በመሆን  እየተሳተፍን መንግስትን እየጠየቅን  ነው።"*

ማታሊን ኮል፣ የላይቤሪያ የቤት ውስጥ ሰራተኞች ህብረት።

8. **የቤት ሰራተኞችን የሚደግፍ ህብረት ጋረ መስራት፣** ወይም አባሎቻቸው የቤት ሰራተኞችን ከሚቀጥሩ ህብረቶች ጋር መስራት። ይህ የቤት ሰራተኛ ድርጅቶችን ለመገንባት እና ከሌሎች ሰራተኞች ጋር ህብረት ለመፍጠር ይረዳል።

9. **በሌሎች ሃገሮች ካሉ ህብረቶች ጋር በመስራት** የቤት ሰራተኞችን በብት ለማረጋገጥ የነበራቸውን ተሞክሮዎች እና መረጃዎች መጋራት። ከስብሰባዎቹ በተጨማሪ፣ ሰራተኞች ቴክኖሎጂ እና ማህበራዊ ድረገጾችን እንደ  ዋትስአፕ (WhatsApp) ቡድኖች፣ ፌስቡክና የዓለም አቀፍ የቤት ሰራቶች ፌደሬሽ  (IDWF) ግንኙነት መፍጠር።

**ለምሳሌ፡**

የ IDWF ግንኙነት ኔትወርክ የተመሰረተው በ 2014 ነው። ግቡም በአለም አቀፍ ያሉ የቤት ሰራተኞችን ማሰባሰብና ወቅታዊ ዜናዎችን፣ እንቅስቃሴዎችን እና መረጃዎችን እንዲጋሩ የሚያደርግ ነው። ኔትወርኩ ለቤት ሰራተኞች ተጨማሪ የመረጃ ምንጭ ነው። (ወደ http://www.idwfed.org/en/campaigns/idwf-new- online-communication-network በመሄድ ኔትወርኩን ያግኙ)።

10. **ከመንግስት ዲፓርትመንቶች እና የአካባቢ ባለስልጣናት ጋር በመስራት** ተቀባይነትን ማበረታታትና ለሰራተኞች ጥበቃ የማድረግን ጥረቶችን መደገፍ (ለምሳሌ፣ ህብረተሰቡ በብዛት በሚሄድባቸው ቢሮዎች ውስጥ የማስታወቂያ ቪዲዮችን መልቀቅ፣ አሰሪዎች ጋር እንዲደርስ የኤሌክትሪክ ክፍያ ወረቀቶች ጋር ብሮሸሮችን ማያያዝ፣ ለልጅ የቤት ሰራተኞች ትምህርት ቤት ውስጥ ትምህርት መስጠት)።

11. **ከአካባቢ እና ማህበረሰብ መሪዎች እና ማህበረሰብ ቡድኖች ጋር መስራት።**

**ለምሳሌ፡**

በኡጋንዳ ውስጥ ያሉ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ቤተክርስቲያን ውስጥ ካሉ ቡድኖች እና ከሴቶች ቡድኖች ጋር በመሆን በበደል ስጋት ውስጥ ያሉ ዋጣት የቤት ሰራተኞችን የመለየት ስራ ይሰራሉ። በታንዛኒያ ውስጥ፣ መንደር ውስጥ ካሉ የሰዎችን ቤት የሚያውቁ ባለስልጣናት ጋር ጋር በመስራት የትኞቹ ቤቶች የቤት ሰራተኛ እንደሚቀጥሩ ማወቅ።

12. **ከፖሊሶች ጋር በመስራት** ስለ የቤት ሰራተኞች ሁኔታ መረዳታቸውን ማረጋገጥ። ይህም ተበደልን የሚሉ የቤት ሰራተኞችን እንዲያግዙ ይረዳቸዋል (ለምሳሌ፣ የኬንያ KUDHEIHA በዚህ መንገድ ከፖሊሶች ጋር ሰርቷል)።

13. **ሰራተኞች ሊያግዙ የሚችሉ ጠበቃዎችን ማግኘት** እና ህጋዊ ሰነዶችን እና ህጋዊ ሂደቶችን እንዲረዱ ማድረግ። እነዚህም ለትርፍ-ያልሆኑ የምርምር ማእከላት፣ የህግ እገዛ ክሊኒኮች፣ ዩኒቨርስቲ ተመራማሪዎች ወይም የምርምር ማእከላት፣ ወይም ፕሮ ቦኖ(ነጻ) አገልግሎት የሚሰጡ የህግ ቢሮዎች ሊሆኑ ይችላሉ። የአካባቢው የዓለም ሥራ ድርጅት ቢሮ፣ ወይም የእርስዎ ህብረት ፌዴሬሽን እርስዎን ሊያግዙ የሚችሉ ጥሩ ጠበቃዎችን ሊጠቁምዎ ይችላሉ። በጠበቃ ወይም/ምርምር ማእከል/የህግ ቢሮ የሚከተሉትን ነገሮች ይፈልጉ፡

- በሰራተኛ ድርጅቶች፣ ባለስልጣናት፣ አሰሪዎች የተከበረ
- በማህበረሰቡ ውስጥ ለድሆች እና ለተጠቁ ሰዎች የሚራራ እና ህይወታቸውን እንዲያሻሽሉ ለሚተጋ፤
- መሪዎቻቸውን ብቻ ሳይሆን ከሰራተኞች ጋር ማውራት እና እነርሱን ማዳመጥ የሚችል፤
- ሴት ሰራተኞች ደፍረው እንዲናገሩ የሚያበረታታ፤
- ለሰራተኞች ነገሮችን በግልጽ ሊያብራራ የሚችል እና በትእግስት ጥያቄዎችን የሚመልስ፤
- ለሰራተኞች አክብሮት ያለውና የሰራተኞችን እውቀት እና እይታ መጠቀም የሚችል፤
- ነጻ (ፕሮ ቦኖ) አገልግሎት የሚሰጥ። ወይም፣ የቀነሰ ክፍያ ለማስከፈል ፍቃደኛ የሆነ።

**ለምሳሌ፡**

የደቡብ አፍሪካ የውስጥ አገልግሎት እና የተባበሩት ሰራተኞች ህብረት (SADSAWU) ከ ማህበራዊ ህግ ፕሮጀክት (SLP) ጋር በዌስተርን ኬፕ ዩኒቨርስቲ ረጅም ጊዜ የቆየ ግንኙነት ነበረው።
SLP SADSAWU ን በ ILO፣ የሰራተኞች የትምህርት መሳሪያዎች ዝግጅት ላይ ፓርላመንቱ እንዲያፈድቀው ስለ C189 የነበረን ውይይት ደግፏል። በ 2016፣ SADSAWU ከ ዊትስ ዩኒቨርስቲ ህግ ክሊኒክ ጋር በመተባበር የቤት ሰራተኞችን በሰራተኛ ካሳ ህግ ስር እንዲታዩ መንግስትን ፍርድ ቤት ወስዷል።

## ማጠቃለያ፡ ስምምነት 189ን እውን ማድረግ

**ደረጃ 1፡ ሃገርዎ ስምምነት 189ን አጽድቃው እንደሆነ ይወቁ**

**ደረጃ 2፡ የማረጋገጫ ዝርዝሩን በመጠቀም በሃገርዎ ያሉትን ክፈተቶች ይፈልጉ**

**ሐገርዎ ስምምነት 189ን ካላጸደቀ፣ ማረጋገጫ ዝርዝሩን የሚጠቀሙት፡**

- በ C189 ላይ ያለውን ክፍተት ለማትናት ወይንም ለመተይቅ፤
- ሃገርዎ ውስጥ ስለ C189 ያለውን የግንዛቤ ክፍተቶችን ለመለየት፤ እና
- ለቤት ሰራተኞች እንደ መማሪያ መሳሪያነት ነው።

**ሃገርዎ C189 ን ካጸደቀ፣ ማረጋገጫ ዝርዝሩን የሚጠቀሙት፡**

- የመንግስት ባለስልጣናት ስለ C189 እንዲያውቁ እንዲገነዘቡ ማድረግ፤
- የመንግስት ሪፖርቶች ላይ አስተያየት ሲሰጡ ወይም መረጃን ለ ILO ሲልኩ፤ እና
- ለቤት ሰራተኞች የግንዛቤ እና ትምህርታዊ መሳሪያ አድርጎ ለመጠቀም።

**ደረጃ 3፡ C189 ን በመጠቀም የቤት ሰራተኞች C189 እንደሚያስፈልጋቸው ጠቅላላ ግንዛቤ አስጨብጡ**

**C189 ን ባጸደቁ ሃገሮች፣ ሰራተኞች ማድረግ የሚችሏቸው ነገሮች፡**

- መንግስት በ C189 ውስጥ ያለውን መብት እንዲሰጣቸው ቅስቀሳ ማድረግ፤
- የቤት ሰራተኞች ላይ ተጽእኖ ስለ ሚፈጥሩ ጉዳዮች ሰራተኞችን ማንቀሳቀስ፤
- ለILO ሪፖርት ማድረግ ሂደት ላይ መሳተፍ፤
- መንግስት ስምምነቱን በመፈጸም ረገድ ILO የሰጠውን አስተያየት ማግኘት፤
- ILO ን መወከለለ እና
- ስለ የመሰብሰብ መብት፣ የመሰብሰብ ነጻነት እና የተውጣጣ ድርድር ቅሬታዎችን ማሰማት።

**C189 ን ባላጸደቁ ሃገሮች፣ ሰራተኞች ማድረግ የሚችሏቸው ነገሮች፡**

- መንግስት ስምምነቱን ለምን እንዳላጸደቀ ማወቅ፤ እና
- አሁን በስራ ላይ ያሉ ህጎችን ተፈጻሚ እንዲያደርግ መንግስትን ቅስቀሳ ማድረግ።

## ደረጃ 3 *(የቀጠለ)*: C189 ን የቤት ሰራተኞች ስለ C189 አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይጠቀሙበት

**ለሁሉም የሰራተኛ ድርጅቶች**

- ቅስቀሳዎችን በማድረግ አጠቃላይ ግንዛቤ ለመፍጠር ሚዲያን መጠቀም።
- ስጋት የሚሆንባቸውን ችግሮች ለመፍታት ሰራተኞችን ማንቀሳቀስ፣ እገዛ ማድረግ እና ማስታጠቅ።
- አሰሪዎች የቤት ሰራተኞች ላይ ያለባቸውን ሃላፊነት ማስተማር
- አንደዳንድ አስተባባሪዎችን/አስተማሪዎችን እንደ ፓራሊጋል (ነጻ) አገልግሎት ሰጪ ማሰልጠን።
- የእርስዎ መንግስት አሁን በስራ ላይ ያሉ ህጎችን እና ፖሊሲዎችን እንዲተገበር ቅስቀሳ ማድረግ።
- ስራዎን ከሚያግዙ ከሁሉም አጋሮች ጋር ስልታዊ ግንኙነቶችን መገንባት፡ ከብሄራዊ ህብረት ፌዴሬሽን፣ በሌላ መስክ ውስጥ ካሉ የሰራተኛ ድርጅቶች፣ በሌላ ሃገር ካሉ የቤት ሰራተኛ ድርጅቶች፣ ህግ ማሻሻል ላይ ከሚሳተፉ ተቋማት ጋር፣ ለምሳሌ፣ የፓርላመንት ፖርፎሊዮ ኮሚቴ፣ ከፖሊስ ጋር፣ ከሌሎች የመንግስት አካላት፣ ከአካባቢ የመንግስት እና ማህበረሰብ መሪዎች እና ከ ጠበቃዎች ጋር።



# ክፍል 4:

# የቅጥር ሞዴል ውል

## ለቤት ውስጥ ሰራተኞች አስተባባሪዎች እና አስተማሪዎች ምክሮች

- ይህ ሞዴል ውል C189 የለያቸውን ችግሮች ለመፍታት ሰራተኞች እና አሰሪዎች ግልጽ ውል እንዲኖራቸው የተዘጋጀ ነው።
- ከብሄራዊ ህጎች አንጻር አንዳንድ ደንቦችን ሊያሻሽሉ ይችላሉ።
- የእርስዎ ሃገር አስቀድሞ ያዘጋጀው የሞዴል ውል ካለ በዚህ ሞዴል ውል ያሉትን እንዲሸፍን መቀየር ይቻል እንደሆነ የሰራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስተሩን ወይም መምሪያውን ያነጋግሩ።
- መንግስት ለቤት ሰራተኞች እና ለአሰሪዎቻቸው ማሰራጨት ይችል ዘንድ የሞዴል ውሉ ቅጂዎች እንዳሉት እርግጠኛ ይሁኑ፣ ለምሳሌ፣ በቢሮዎቻቸው እና በቤት ውስጥ ምርመራ በሚያካሂዱበት ወቅት።
- ሰራተኛው የውሉን ቅጂ መቀበሉን ወይም በሚረዱት ቋንቋ ግልጽ መደረጉን እርግጠኛ ይሁኑ።

## ለቤት ሰራተኞች ምክሮች

1. ከ 1-13 ያሉት የሚሸፍኑት በ C189 አንድ የቅጥር ውል መሸፈን ያለባቸውን ነገሮች ነው። ውሉ ውስጥ መካተት የሚገባቸውን ጉዳዮች ለመለየት እንደ ማመሳከሪያነት ይጠቀሙበት።
2. ለእርስዎ የማይተገበሩ አንቀጾችን ይሰርዙ። ለምሳሌ፣ የቤት ሰራተኛው ከሌላ ሃገር የመጣ ካልሆነ፣ አንቀጽ 13 መተው ይችላሉ።
3. ምርጫ ያላቸው አንቀጾችም ተዘርዝረዋል። እነዚህ በ C189 የሚሸፈኑ አይደሉም፣ ነገር ግን የሚደራደሩ ከሆነ ጥሩ አንቀጾች ናቸው። Recommendation 201 በሞዴል ውሉ ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ አንቀጾችን ይዘረዝራል (ማጣቀሻ 1 ን ይመልከቱ)። በአለም አቀፍ ዙሪያ ካገኘናቸው ሞዴል ውሎች ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ምርጫ ያላቸው አንቀጾችንም ዘርዝረናል (ማጣቀሻ 2 ን ይመልከቱ)።




4. የሞዴል የሰአት መቆጣተሪያ እና የክፍያ ማረጋገጫ ደረሰኝም የስራ ሰአትዎን እንዲመዘግቡ እና ክፍያዎችን እና ተቆራጮችን እንዲቆጣጠሩ አካተናል። (ማጣቀሻ 3 ን ይመልከቱ)።

# ለቤት ውስጥ አገልግሎቶች የቅጥር ውል

## መግቢያ

አሰሪው እና የቤት ሰራተኛው ለቤት ውስጥ ስራ የስራ ቅጥር ውል ለማርቀቅ ተስማምተዋል።

የሚከተሉት ህጎች እና/ወይም የጋራ ስምምነቶች ይህን ውል ይቆጣጠራሉ፡

________________________________________

________________________________________

________________________________________

## የውሉ ወገኖች

**የውሉ ወገኖች**

**የአሰሪው ስም፡** ______________________________

መታወቂያ ቁጥር______________________________

ስልክ ቁጥር______________________________

አድራሻ፡ ______________________________

________________________________________

**የሰራተኛው ስም፡** ______________________________

መታወቂያ ቁጥር______________________________

ስልክ ቁጥር______________________________

አድራሻ፡ ______________________________

________________________________________

የትውልድ ቀን፡ ______________________________

## የውሉ አይነት

1 **የስራ መጠሪያ:** ______________________________

2 **የውሉ አይነት እና ጊዜ ገደብ**

የቤት ውስጥ ሰራተኛው የሚቀጠረው

☐ ለተወሰነ ጊዜ ☐ ላልተወሰነ ጊዜ

የቤት ውስጥ ሰራተኛው ከ______________________________እስከ________ ይቀጠራሉ

የቤት ውስጥ ሰራተኛው የሚሰራው በ

☐ በትርፍ ጊዜ ☐ ሙሉ ጊዜ እና በሳምንት ለ__________________ቀናት ነው።

3 የሙከራ ጊዜ ገደብ

የመጀመሪያዎቹ____________ቀናት የሙከራ ቀናት ይሆናሉ።

## ስራ የሚሰራበት ቤትና ተግባራት

4 ***የቤቱ አድራሻ***

ሰራተኛው በዚህ አድራሻ ይሰራል: ______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

5 ***የቤት ሰራተኛው ተግባራት***

የሰራተኛው ተግባራት የሚከተሉት ናቸው:

☐ ጽዳት ☐ ልዩ ኩነቶች

☐ አዛውንቶችን/የታመሙትን/አካለ ስንኩላንን መንከባከብ ☐ ማብሰል

☐ ጉዞዎች/በአላት ☐ የቤት እንስሳ መንከባከብ ☐ ላውንደሪ ☐ ልጅ መንከባከብ

☐ አትክልት መንከባከብ ☐ ተሽከርካሪ መኪና

## ክፍያ እና ክፍያዎች

### 6 ክፍያ

አሰሪው ለቤት ሰራተኛው የሚከፍለው ክፍያ ________________________________________በ___________ነው።

አሰሪው ለቤት ሰራተኛው

☐ በየሳምንቱ ☐ በየምሽቱ ☐ በየወሩ

አሰሪው ለቤት ሰራተኛው የሚከፍለው

☐ በካሽ ☐ በባንክ ማስቀመጥ ☐ በባንክ ቼክ

## የስራ ሰአት

### 7 የስራ ሰአታት እና የቀን የእረፍት ጊዜያት

የቤት ውስጥ ሰራተኛው በአጠቃላይ ለ ___________________________________ሰአት በቀን እና_

____________________ሰአት በሳምንት ይሰራል።

ከታች ያለውም ሰንጠረዥ የቤት ውስጥ ሰራተኛውን በየቀኑ የስራ መጀመሪያ፣ ማብቂያ እና የእረፍት ጊዜዎች ይዘረዝራል።

| ቀን | የመጀመሪያ ሰአት | እረፍቶች | የማብቂያ ሰአት |
|---|---|---|---|
| እሁድ | | | |
| ሰኞ | | | |
| ማክሰኞ | | | |
| እሮብ | | | |
| ሀሙስ | | | |
| አርብ | | | |
| ቅዳሜ | | | |

የቤት ውስጥ ሰራተኛው በቀን ቢያንስ ለ __________________________________________________ሰአት
የሚሆን እረፍት መውሰድ አለበት

### 8 ሳምንታዊ የእረፍት ጊዜያት

የቤት ውስጥ ሰራተኛው ቢያንስ____________________________________ያልተቋረጠ ሰአታት
የእረፍት ጊዜ በሳምንት መውሰድ አለበት፣ መደበኛው የእረፍት ቀን _____________________ይሆናል።

## የአመት ፍቃድ

### 9 *የአመት ፍቃድ*

የቤት ሰራተኛው አንድ አመት ካገለገለ በኋላ የሚከተለውን የአመት ፍቃድ ማግኘት ይችላል፡

_______________ ቀናት የአመት ፍቃድ/በአል።

ሁለቱ ወገኖች  የአመት ፍቃዱ መቼ እንደሚጀመር ይስማማሉ።

## የመኖሪያ ዝግጅቶች

### 10 *ማረፊያ ቦታ*

አሰሪው ለቤት ሰራተኛው ማረፊያ ቦታ ያዘጋጃል።

☐ አዎ ☐ አይ

### 11 *የየቀን ምግቦች*

አሰሪው ለቤት ውስጥ ሰራተኛው በየቀኑ ለ ______________________________ ጊዜ ምግብ መስጠት አለበት።

## ውሉን ማቋረጥ

### 12 የማቋረጫ ማሳወቂያ

አሰሪው ለቤት ሰራተኛው ______________________________________________________ቀን

________________ ሳምንት______________________ወር ቀድሞ ማሳወቂያ መስጠት አለበት፣ ወይም
የቅጥር ማቋረጫ፣ ወይም ማሳወቂያ ከመስጠት ይልቅ የቤት ሰራተኛውን መክፈል።

የቤት ሰራተኛው ለአሰሪው______________________________________________________ቀን

________________ ሳምንት______________________ወር ቀድሞ ማሳወቂያ መስጠት አለበት።

አሳማኝ ምክንያት ካለ የማቋረጫ ማሳወቂያ መስጠት አስፈላጊ አይደለም፣ ለምሳሌ፣ ሰራተኛው ከአሰሪው እቃ ከሰረቀ፣ ወይም አሰሪው ሰራተኛውን የሚበድል ከሆነ።

### በውሉ መቋረጥ ላይ ወደ ሃገር መመለስ

የቅጥር ግንኙነቱ ሲቋረጥ፣ ሰራተኛው ወደ ቤቱ የመመለሻ ወጪው መክፈል ያለበት በአሰሪው ነው።

☐ አዎ ☐ አይ

## የወገኖቹ ፊርማ

የሰራተኛው ፊርማ: ______________________________________________

ቀን እና ቦታ: ______________________________________________

የአሰሪው ፊርማ: ______________________________________________

ቀን እና ቦታ: ______________________________________________

የምስክር ፊርማ ______________________________________________

ቀን እና ቦታ: ______________________________________________

## ማጣቀሻ 1፡ በምክረሃሳብ 201 ላይ አማራጭ አንቀጾች

በምክረሃሳብበምክረሃሳብ 201 የሚመክረው አንድ ሞዴል ውል C189 ከሚጠብቃቸው አንቀጾች ሌላ ተጨማሪ አንቀጾችን እንዲያካትት ነው።

### 1. በአይነት የሚደረጉ ክፍያዎች

አሰሪው ለቤት ሰራተኛው እስከ ________________________________________ ፐርሰንት ያለውን ክፍያውን በአይነት መክፈል አለበት።

አሰሪው ለሰራተኛው መስጠት ያለበት (እቃዎቹን እና ብዛታቸውን ግለጽ)

________________________________________ የሚገመተው ____________________

________________________________________ የሚገመተው ____________________

________________________________________ የሚገመተው ____________________

### 2. ሌሎች ክፍያዎች

አሰሪው ለሰራተኛው ከሚከፍለው ከመደበኛ ክፍያው በተጨማሪ ለሰራተኛው የሚከተሉትን መክፈል አለበት፡

__________ በ____________ ለ ________________________________________

__________ በ____________ ለ ________________________________________

__________ በ____________ ለ ________________________________________

### 3. ተጨማሪ ሰአት ስራ

አሰሪው ለቤት ሰራተኛው ለእያንዳንዱ የተጨማሪ ሰአት ስራ __________________________ መክፈል አለበት።

### 4. ተጠባባቂ

አሰሪው ለቤት ሰራተኛው ለእያንዳንዱ ተጠባባቂ ጊዜ ______________________________ መክፈል አለበት።

### 5. የደምቀዝ ተቀናሾች

አሰሪው ከቤት ሰራተኛው ክፍያ ላይ የሚከተለውን መጠን ሊቀንስ ይችላል።

____________ ለጤና ኢንሹራንስ/ህክምና እርዳታ

____________ ለማህበራዊ ደህንነት (ስራ አጥ ኢንሹራንስ/ጡረታ)

____________ ለግል የስልክ ጠሪዎች

የቤት ውስጥ ሰራተኛው እቃዎችን ከሰበረ አሰሪው ገንዘብ ላይቀንስ ይችላል።

## 6. የማረፊያ ቦታ ዝርዝሮች

አሰሪው ለሰራተኛው ምቹ እና ንጹህ የሆነ የሚከተሉትን የሚያሟላ ማረፊያ ቦታ ማዘጋጀት አለበት፡

- በቁልፍ መዘጋት የሚችል ክፍል
- አልጋ እና ፍራሽ
- ኤሌክትሪክ እና ማሞቂያ
- አየር ማናፈሻ
- ንጹህ የመጠጥ ውሃ
- የሚቆለፍ የባኞ ቤት እና የገላ መታጠቢያ

## 7. ሌላ ፍቃድ አይነቶች

የቤት ውስጥ ሰራተኛው የአንድ አመት አገልግሎት ከሰጠ በኋላ የሚከተሉትን ፍቃዶች ማግኘት ይችላል፡

________________ የህመም ቀን ፍቃድ፣

________________ የቤተሰብ ሃላፊነት ፍቃድ፣

________________ የጥናት ፍቃድ፣

________________ የእናቶች የወሊድ ፍቃድ፣ ከዚህ ውስጥ____________________________ተከፋይ የሚሆን።

## ማጣቀሻ 2: በብሄራዊ ሞዴል ውሎች አማራጭ አንቀጾች

በአለም አቀፍ ዙሪያ ካገኘናቸው ለቤት ሰራተኞች ሞዴል ውሎች ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ አንቀጾችንም አካተናል። ምንም እንኳን C189 እና ምክረሃሳብ 201 እነዚህ ጉዳዮች በቅጥር ውል ውስጥ እንዲካተቱ ባይጠይቁም፣ ሃገርዎ ውስጥ ባለ ሞዴል የቅጥር ውል ውስጥ ከእነዚህ የትኛውን እንደሚያስገቡ ማሰብ አለብዎ። እንደ ሰራተኛም የትኞቹ አንቀጾች ለእርስዎ ጠቃሚ እንደሆኑ ማሰብ እና ከአሰሪዎ ጋር በጊዜ ሂደት መደራደር መሞከር።

### 1. የውሉን ደንቦች መቀየር

ሁለቱ ወገኖች በጽሁፍ የውሉን ደንቦች ለመቀየር መስማማት አለባቸው።

### 2. የክፍያ ጭማሪዎች

በቅጥሩ በእያንዳንዱ አመት መጨረሻ ላይ አሰሪው የሰራተኛውን ክፍያ በ ____________________ ፐርሰንት መጨመር አለበት።

### 3. ልብስ

አሰሪው ለሰራተኛው በነጻ የስራ ደንብ ልብስ መስጠት አለበት።

### 4. በስራ ቦታ ጤንነት እና ደህንነት

አሰሪው ማድረግ ያለበት፡

- መከላከያ ልብስ እና መሳሪያዎች በነጻ መስጠት፣
- በስራ ቦታ የራሳቸውን ጤንነት እና ደህንነት እንዴት እንደሚጠብቁ ማስተማር (ለምሳሌ፣ ማሺኖችን እና ኬሚካሎችን እንዴት እንደሚጠቀሙ ማሳየት)፣
- ሃገሩ ህጉ ካለው የስራ ጉዳቶች ወይም በሽታዎችን ለመሸፈን ሰራተኛውን ማስመዝገብ።

### 5. በድንገተኛ ጊዜዎች እገዛ

☐ አሰሪው የመጀመርያ እርዳታ ኪት መስጠት አለበት።

☐ በቅርብ ያለው የፖሊስ ጣቢያ እና የህክምና አገልግሎት ዝርዝር አሰሪው መስጠት አለበት።

☐ አሰሪው ለቤት ሰራተኛው በድንገተኛ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል አደጋ ጊዜ ተጠሪ መስጠት አለበት።

## 6. የሰራተኛው ጉዞ

አሰሪው

- [ ] ለሰራተኛው ስለ ጉዞ እቅዶች ____________ ማሳወቂያ መስጠት አለበት።
- [ ] ሰራተኛው ካሰሪው ጋር በሚሄድበት ጊዜ ጉዞውን በተመከከተ የትኛውንም ወጪ አሰሪው መሸፈን አለበት።
- [ ] ሰራተኛው ከአሰሪው ጋር አብሮ የማይጓዝ ቢሆንም እንኳን አሰሪው ለሰራተኛው መክፍል አለበት።

## 7. ሳምንታዊ የእረፍት ጊዜያት

የቤት ውስጥ ሰራተኛው ቢያንስ ____________________________________ ያልተቋረጠ ሰአታት የእረፍት ጊዜ በሳምንት መውሰድ አለበት፣ እና መደበኛው የእረፍት ቀን

__________________________________________________________________ይሆናል።

## 8. የህዝብ በአላት

በመደበኛ የስራ ቀናት ላይ የሚያርፉ ብሄራዊ/የህዝብ በአላት ላየ አሰሪው ለቤት ሰራተኛው ከክፍያ ጋር የእረፍት ቀን ይሰጣል።

በብሄራዊ/የህዝብ በአላት ሰራተኛው የሚከፈለው ለስራ በሰአት/በቀን

____________________________________________________

ያህል ነው።

## 9. ውል ማቋረጥ ላይ ያሉ ጥቅማ ጥቅሞች

ውሉ ሲቋረጥ አሰሪው ለሰራተኛው መክፈል ያለበት ________________ ነው።

## 10. አመታዊ ስጦታ (ቦነስ)

አሰሪው ለሰራተኛው እስከ________የሳምንት/የወር ክፍያ የሚደርስ አመታዊ ስጦታ (ቦነስ) መስጠት አለበት።

## ማጣቀሻ 3: ወርሃዊ የጊዜ መቆጧተሪያ እና የክፍያ ማረጋገጫ ደረሰኝ

ወርሃዊ የሰአት መቆጣጠሪያ እና የክፍያ ማረጋገጫ ደረሰኝ

ከ____________________ለ ________________

ስም፡ ______________________________________________________________________

| ቀናት | | የስራ ሰአታት | | | ጠቅላላ ሰአታት | | | | የማብቂያ ሰአት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቀን | የሳምንቱ ቀን | መጀመሪያ | እረፍት | ማብቂያ | በየቀኑ | በመደበኛ | ተጨማሪ ሰአት ስራ | አመት በአል | መደበኛ (ሰአታት x ) | ተጨማሪ ሰአት(ሰአታት x ) | አመት በአል (ሰአታትx ) | ጠቅላላ |
| 1ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 2ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 3ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 4ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 5ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 6ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 7ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 8ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 9ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 10ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 11ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 12ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 13ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 14ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 15ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 16ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 17ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 18ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 19ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 20ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 21ኛ | | | | | | | | | | | | |

| ቀናት | | የስራ ሰአታት | | | ጠቅላላ ሰአታት | | | | የማብቂያ ሰአት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቀን | የሳምንቱ ቀን | መጀመሪያ | እረፍት | ማብቂያ | በየቀኑ | በመደበኛ | ተጨማሪ ሰአት ስራ | አመት በአል | መደበኛ (ሰአታት x ) | ተጨማሪ ሰአት(ሰአታት x ) | አመት በአል (ሰአታትx ) | ጠቅላላ |
| 22ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 23ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 24ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 25ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 26ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 27ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 28ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 29ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 30ኛ | | | | | | | | | | | | |
| 31ኛ | | | | | | | | | | | | |
| አጠቃላይ መደበኛ ክፍያ | | | | | | | | | | | | |
| ቅናሽ 1፡ | | | | | | | | | | | | |
| ቅናሽ 2፡ | | | | | | | | | | | | |
| ቅናሽ 3፡ | | | | | | | | | | | | |
| አጠቃላይ ቅናሾች፡ | | | | | | | | | | | | |
| ወደ ቤት የሚወሰድ ክፍያ | | | | | | | | | | | | |

ተከፍሏል (በአሰሪው የሚከፈል)

ቀን፡____________________

ቦታ፡ ____________________

ተቀብሏል (በሰራተኛው የሚፈረም)

ቀን፡____________________

ቦታ፡ ____________________

# ክፍል 5:

# ሌሎች መጠቀም የሚችሏቸው ግባአቶች

ስለ C189 የሚናገረውን ይህን በራሪ ጽሁፍ ማንበብ የቤት ውስጥ ሰራተኞችን በትክክል ለማስተባበር እና የተሻለ መብቶችን ለማስሸፈን ይረዳዎታል። ይህ ክፍል ይህንን መመሪያ ስናዘጋጅ የተጠቀምናቸውን ግብአቶች ይዘረዝራል። ስለ C189 ያለዎትን ግንዛቤን ለመጨመር እና ድርጅትዎን ለመገንባት ሊያነቧቸው ይችላሉ።

## በ C189 ላይ ያሉ ግብአቶች


1. Celia Mather ***'Yes, we did it!' How the World's Domestic Workers Won their International Rights and Recognition*** (2013)
   http://www.wiego.org/resources/yes-we-did-it-how-worlds-domestic-workers-won-their-international-rights-and-recognition
2. ***C189: Conventional Wisdom,*** a documentary film on C189 by the International Domestic Workers' Federation and WIEGO
   http://www.wiego.org/resources/video-c189-conventional-wisdom
3. International Labour Office, Geneva. ***C189 and R201 at a Glance*** (2011)
   http://www.ilo.org/wcmsp5/groups/public/@ed_protect/@protrav/@travail/documents/publication/wcms_170438.pdf
4. International Labour Office, Geneva. ***Effective Protection for Domestic Workers: A Guide to Designing Labour Laws***
   http://www.ilo.org/travail/areasofwork/domestic-workers/WCMS_173365/lang--en/index.htm
5. International Labour Office, Geneva. ***Achieving Decent Work for Domestic Workers: An Organizers' Manual to Promote C189 and Build Domestic Workers' Power*** (2012)
   http://www.ilo.org/wcmsp5/groups/public/---ed_dialogue/---actrav/documents/publication/wcms_181344.pdf
6. International Trade Union Confederation, International Domestic Workers' Federation and International Labour Organization. ***Domestic Workers Unite: A Guide For Building Collective Power to Achieve Rights and Protections for Domestic Workers*** (2013)
   https://www.ituc-csi.org/IMG/pdf/ituc-domesticworkersunite-final-en-final_digital.pdf

## ማስተባበር ላይ ያሉ ግብአቶች

*ሰራተኞችን ስለማስተባበር በ WIEGO የታተሙ ሌሎች ቡክሌቶችን ማንበብዎን እርግጠኛ ይሁኑ። ከታች ያለው መጽሐፍ 1 የሚያወራው እያስተባበሯቸው ያሉትን ሰራተኞች ላይ ተጽእኖ ስለሚያደርጉ ህጎች እና ደንቦች ላይ ምርምር የመስራትን ጥቅም ነው።*

**መጽሐፍ 1፡ *Recruiting Informal Workers into Democratic Workers' Organisations***
http://www.wiego.org/sites/default/files/resources/files/ICC1-Recruiting-Informal-Workers-Orgs-English.pdf

**መጽሐፍ 2: *Building and Maintaining a Democratic Organisation of Informal Workers***
http://www.wiego.org/sites/default/files/resources/files/ICC2-Building-Orgs-Informal-Workers-English.pdf

**መጽሐፍ 3: *Handling the Day-To-Day Problems of Informal Workers***
http://www.wiego.org/sites/default/files/resources/files/ICC3-Handling-Problems-English.pdf

**መጽሐፍ 4: *Collective Negotiations for Informal Workers***
http://www.wiego.org/sites/default/files/resources/files/ICC4-Collective-Bargaining-English.pdf

**መጽሐፍ 5: *Handling Disputes between Informal Workers and those in Power***
http://www.wiego.org/sites/default/files/resources/files/ICC5-Disputes-English.pdf

**መጽሐፍ 6: *Collective Action for Informal Workers***
http://www.wiego.org/sites/default/files/resources/files/ICC6-Collective-Action-English.pdf

## አባሪ፡

# ILO ምክረሃሳብ ቁ. 201 ምንድነው?

- የ ILO ምክር ሃሳቦች ስምምነትን እንዲተገብሩ የሚረዳ መመሪያ ነው።
- ምክረሃሳቦች ቁ. 201 (ወይም R201) አባል ሃገራትን C189 ን እንዴት መተግበር እንዳለባቸው መመሪያ ይሰጣል። ከ C189 የሚለየው መጽደቅ ስለሌለበት እና በአባል ሃገራት ብቻ የተወሰነ አለመሆኑ ነው።

የተወሰኑ የ C189 ክፍሎችን መተግበር ከፈለጉ መንግስት ምን ማድረግ እንዳለበት ለማብራራት R201 ን መጠቀም ይችላሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ተመሳሳይ ችግርን ለመፍታት በተለያዩ መንገዶች ያብራራል።

እንደ C189፣ የሚከተሉትን ይሸፍናል፡

- መሰረታዊ መብቶች፤
- የስራ ቅጥር ውል፤
- መሰረታዊ የመስሪያ ሁኔታዎች
- ጤንነት እና ደንንነት በስራ ቦታ፤
- ማህበራዊ ደህንነት፤
- ለቤት ሰራተኞች ጥበቃ የማድረግ እርምጃዎች፣ በተለይም ስደተኛ የቤት ውስጥ ሰራተኞች፤
- የቅጥር ኤጀንሲዎችን መቆጣተር።

በተጨማሪም ሌሎች መብቶችን ይሸፍናል።
ምክረሃሳብ 201 የሚለው የሚከተለውን
ነው፡

## ሀ). መሰረታዊ መብቶች

***አባል ሃገራት ማድረግ ያለባቸው ነገሮች፡***

- የቤት ሰራተኞች የራሳቸውን ድርጅቶች እንዲያቋቁሙ ወይም የሚፈልጉትን ድርጅት እንዲቀላቀሉ ያሉት ህጎች እና ሂደቶች ቀላል መሆናቸውን እርግጠኛ መሆን።
- የቤት ሰራተኛ ድርጅቶች እንዲጠነክሩ ማገዝ።
- የቤት ሰራተኞች የህክምና መረጃን ለመጠበቅ ህግ ማውጣት እና ለስራ አላማ የህክምና ምርመራ ማድረግ ያለባቸውን ሰራተኞች መጠበቅ።
- ሰራተኞች በግድ የ የኤችአይቪ ምርመራ ወይም የእርግዝና ምርመራ እንዳያደርጉ መጠበቅ ወይም ለአሰሪያቸው የ የኤችአይቪ ወይም የእርግዝና ሁኔታቸውን እንዲነግሩ ከመገደድ መጠበቅ።
- የቤት ሰራተኞችን ሊያጠቃ የሚችል በሽታ ካለ ማጋራት እና ለጥሩ ጤና ልምምዶች መመሪያዎች እና ከስራ ጋር የተገናኙ የጤና ምርመራዎች ማድረግ።
- ልጆች ጤናቸውን፣ ደህንነታቸውን እና ሞራላቸውን ሊጎዱ የሚችሉ የቤት ውስጥ ስራዎችን እንዳይሰሩ ማረጋገጥ።

- እድሜያቸው ከ 15 አመት በላይ የሆኑ ልጆች የቤት ሰራተኞች የሚሰሩበትን የስራ ሰአታት መገደብ፣ በምሽት እንዳይሰሩ ማድረግ፣ ከባባድ ስራዎችን እንዳይሰሩ ማድረግ። መንግስታት የልጆችን የስራ እና የኑሮ ሁኔታ ማየት አለባቸው።
- ቅሬታ ማስገቢያ መንገዶችን መፍጠር እና ለተሰቃዩ፣ በደል ለደረሰባቸው እና መጥፎ እንክብካቤ ለነበሩ የቤት ውስጥ ሰራተኞች ጊዜያዊ መጠለያ እና የጤና እንክብካቤ መስጠት።

## ለ). የስራ ቅጥር ውል

***አባል ሃገራት ማድረግ ያለባቸው ነገሮች፡***

- የቤት ሰራተኞች የቅጥር ደንብ እና ሁኔታዎችን እንዲረዱ ማገዝ።
- ለአሰሪዎች፣ ለሰራተኞች እና ለማህበረሰቡ በነጻ ሊገኝ የሚችል ሞዴለ የቅጥር ውል ማዘጋጀት።
- በ C189 ካሉ ጉዳዮች በተጨማሪ፣ የቅጥር ደንቦች እና ሁኔታዎች የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፡
  - የስራ ዝርዝር መግለጫ፤
  - የህመም ፍቃዶች እና ሌሎች የግል ፍቃዶች፣
  - የቤት ሰራተኛው የመቀበል መብት ያለው የትኛውም አይነት ክፍያዎች፤
  - በአይነት የሚከፈሉ ክፍያዎች እና የሀገንዘብ ዋጋ ተመኑ፤
  - የተሰጠው ማረፊያ ዝርዝር፤
  - አሰሪው ከሰራተኛው ደምወዝ ላይ መቀነስ የሚችለው መጠን።

## ሐ). መሰረታዊ የስራ ሁኔታዎች

***አባል ሃገራት ማድረግ ያለባቸው ነገሮች፡***

- አሰሪዎች እና ሰራተኞች የስራ ሰአታትን፣ ተጨማሪ የስራ ሰአታትን እና የተጠባባቂ ጊዜዎችን እንዲመዘግቡ ማገዝ። የቤት ውስጥ ሰራተኞች እነዚህን ሪከርዶች በቀላሉ ማግኘት አለባቸው።
- ከፍተኛ የተጠባባቂ ሰአታት በሳምንት፣ በወር ወይም በአመት በማስቀመጥ የጥሪ ጊዜያትን እና ለተጠባባቂ ጊዜ ክፍያዎችን መቆጣጠር። ሰራተኞች እያረፉ የተጠባባቂ ጊዜ ላይ ከሆኑ የእረፍት ጊዜ ማግኘት አለባቸው።
- ከፍተኛ የምሽት ሰአታት፣ ለምሽት ስራዎች የክፍያ መጠን እና በእረፍት ወቅት የምሽት ስራ በመስራት የእረፍት ጊዜ ማግኘትን መቆጣጠር።

- እንደ የቤት ሰራተኛው የባህል፣ የማህበራዊ እና የሃይማኖታዊ መስፈርት እንጻር ወገኖቹ በሳምንታዊው የእረፍት ቀን ላይ መስማማት አለባቸው።
- ሰራተኞች ቢከፈላቸውም ባይከፈላቸውም በእረፍት ቀናቸው ለሰሩት ስራ ማካካሻ የእረፍት ቀን እንዲወስዱ ማረጋገጥ።
- ሰራተኞች ሳምንታዊ የስራ ቀኖቹን ማጠራቀም እንዲችል ይህም 14 ቀን ሰርቶ የተጠራቀመ እረፍት ቀናት እንዲወስዱ መፍቀድ።
- አሰሪዎች የቤት ሰራተኛውን በበአሉ ቀን በሚወስደው ጊዜ አሰሪው የቤት ሰራተኛውን የእረፍት ቀናት አይቀንስም።
- በአይነት የሚከፈለውን መጠን መገደብ፣ የክፍያ ዋጋ ተመኑ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መሰላቱን ማረጋገጥ እና የቤት ሰራተኛው የሚፈልጋቸውን እና የሚጠቀምባቸውን ነገሮች ብቻ እንዲከፈለው መገደብ።
- አሰሪዎች በቤት ውስጥ ነዋሪ የሆኑትን የቤት ሰራተኞች ለማረፊያ እንደማያስከፍሉ ማረጋገጥ።
- አሰሪው ሰራተኞች ስራቸውን ለማከናወን በሚያስፈልጋቸው ነገሮች ላይ ክፍያ አለመጠየቁን ማረጋገጥ (ለምሳሌ፣ የደንብ ልብስ፣ መሳሪያዎች፣ ጓንት፣ ወዘተ.)።
- አሰሪዎች ለቤት ሰራተኞች በከፈሏቸው ቁጥር የክፍያ ማረጋገጫ ደረሰኝ መስጠታቸውን ማረጋገጥ። የክፍያ ማረጋገጫ ደረሰኙ አጠቃላይ መጠኑን እና ምንም አይነት ተቀናሽ እንዳለ ማስረዳት አለበት።
- ሰራተኞች የግል ባኞ ቤት፣ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች፣ መስኮት እና በቂ ብርሃን እና የአየር ሙቀት መቆጣጠሪያ እንዳላቸው ማረጋገጥ። ክፍሉ መቆለፊያ ያለውና ሰራተኛው የራሱ ቁልፍ ሊኖረው ያስፈልጋል። ሰራተኛው ሽንት ቤት እና ባኞ ቤት መጠቀም መቻል አለበት።
- አሰሪዎች የሰራተኞችን የሃይማኖት እና የባህል ፍላጎት የሚያሟሉ ጥሩ እና በቂ ምግብ መስጠታቸውን ማረጋገጥ።

## መ). የስራ ቦታ ደህንነት እና ጤንነት

***አባል ሃገራት ማድረግ ያለባቸው ነገሮች፥***

- የቤት ሰራተኞችን በስራ ቦታ ካሉ አደጋዎች እና ስጋቶች መጠበቅ።
- የስራ ቦታዎችን መገምገም የሚችሉባቸውን መንገዶች መፍጠር እና የጤና እና የደህንነት ህጎችን የሚጥሱ አሰሪዎችን መቅጣት።
- አደጋ የደረሰባቸውን እና በስራ ቦታ በበሽታ ስለተያዙ የቤት ሰራተኞችን መረጃ መሰብሰብ።
- በስራ ቦታ ስላለው ደህንነት እና የጤንነት ሁኔታ ለቤት ሰራተኞች ምክር እና መረጃ መስጠት።

## ሠ). ማህበራዊ ደህንነት

***አባል ሃገራት ማድረግ ያለባቸው ነገሮች፡***

- የማህበራዊ ደህንነት መዋጮ መክፈልን ቀላል ማድረግ፣ ከአንድ በላይ አሰሪ ያላቸውን ሰራተኞች ጭምር።
- ከሌሎች ሃገራት ጋር በመስራትም በሌላ ሃገር ጥቅማ ጥቅም ማግኘት ያለባቸው የቤት ሰራተኞች በሚኖሩበት ሃገር ማግኘት እንዲችሉ ማድረግ።
- ድጎማዎችን እና ጥቅማ ጥቅሞችን ሲያሰሉ ለሰራተኘው የሚከፈለውን የተጣራ ክፍያ (በእጅ የሚገባ ክፍያ) ያስቡ።

## ረ). ለቤት ሰራተኞች ጥበቃ የማድረግ እርምጃዎች፣ በተለይም ስደተኛ የቤት ውስጥ ሰራተኞች፤

***አባል ሃገራት ማድረግ ያለባቸው ነገሮች፡***

- ላኪ ሃገሮች ከሆኑ፣ ስደተኛ የቤት ሰራተኞች ከመሄዳቸው በፊት በሚሰሩበት ሃገር ስላሉ መብቶች ማወቅ እና ስለ መፍትሄያቸው በሚረዱት ቋንቋ ማወቅ አለባቸው።
- የቤት ሰራተኞች በምን ሁኔታ ውስጥ ውላቸው ሲያልቅ ወደ መጡበት ሃገር በነጻ ትራንስፖርት መመለስ እንደሚችሉ ግልጽ የሆኑ መመሪያዎችን መመስረት።

***አባላ ሃገራት ማሰብ ያለባቸው ነገሮች፡***

- እርዳታ ለሚፈልጉ ሰራተኞች ብሄራዊ የጥሪ መስመሮችን በተለያየ ቋንቋ ማዘጋጀት።
- ስደተኛ የቤት ሰራተኞች ስራ ከመጀመራቸው በፊት የሚሰሩበትን ቤት መጎብኘት እንዲችሉ መፍቀድ።
- ለአስቸኳይ ቢዜ ድንገተኛ ጉዳይ የሚውል የቤቶች ኔትወርክ መገንባት።
- አሰሪዎች የቤት ሰራተኞች ላይ ያለባቸውን ሃላፊነት ማስተማር፣ ስደተኛ የቤት ሰራተኞችን ጨምሮ።
- የቤት ሰራተኞች አሰሪያቸው ላይ በቀላሉ ቅሬታ ማቅረብ እንዲችሉ እና አሰሪዎቻቸውንም ፍርድ ቤት መውሰድ እንዲችሉ፣ ወደ ቤታቸው ከተመለሱ በኋላ እንኳን፣ ቀላል ማድረግ።
- ወደ ሌላ ሃገር ለስራ ከመነሳታቸው በፊት ስደተኛ ሰራተኞች መብታቸውን ለመንገር ከሌሎች ሃገሮች ጋር አብሮ መስራት።
- ለሰራተኞች የፍርድ ቤት ወጪዎች የተወሰነ ገንዘብ ማስቀመጥ እና ማህበራዊ አገልግሎቶችን መስጠት።
- መርማሪዎችም የአሰሪውን ግላዊ ሙብት ባከበረ መልኩ ወደቤት ሰራተኛው የስራ ቦታ በመሄድ መመርመር የሚያስችሉ ህጎችን ማዘጋጀት።
- የቤት ሰራተኛ ለሚቀጥሩ ዲፕሎማቶች የምግባር ደንቦችን ማዘጋጀት።

## ረ). የቅጥር ኤጀንሲዎችን መቆጣጠር

- አባል ሃገራት ከሌሎች ሃገራት ጋር በመስራት የቅጥር ኤጀንሲዎችን መቆጣጠር አለባቸው።

## ሸ). የቤት ሰራተኞች ላይ ተጽእኖ ለሚያመጡ ለሌሎች ጉዳዮች መፍትሄ መስጠት

***አባል ሃገራት ማድረግ ያለባቸው ነገሮች፡***

- አሰሪው የሞተበት ወይም ክፍያውን መክፍል ያልቻለ የቤት ሰራተኛ በሌላ መስክ እንዳሉ ሰራተኞች ተመሳሳይ መብቶች አሉት።
- የስራ ቅጥር ውሉ እንዳለቀ በቶሎ አሰሪዎች ለቤት ሰራተኞች ያልተከፈለ ክፍያዎችን መክፈል አለባቸው።
- ቅጥሩን የሚያቋርጥ አንድ አሰሪ ( ከከፍተኛ የምግባር ደንብ ጥሰት ውጪ) በቤት ውስጥ ለሚኖረው የቤት ሰራተኛ በቂ የማሳወቂያ ጊዜ እና ሌላ ስራ የሚፈልግበትን ጊዜ እንዲሁም የመቆያ ስፍራ መስጠት አለበት።
- ክህሎታቸውን እና ስራ መቀጠራቸውን ለማሳደግ የቤት ሰራተኞች ስልጠናን ማበረታታት።
- የቤት ሰራተኞችን ስራ እና የቤተሰብ ሃላፊነቶች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ እንዲይዙ መርዳት።
- በቤት ውስጥ ስላለ ስራ የሚሰበስቡትን መረጃ ስርአት ማሻሻል።

## ቀ). አባል ሃገራት ይህን ምክር እንዴት ተግባር ላይ ማዋል ይችላሉ?

***የቤት ሰራተኞችን ለመጠበቅ፣ አባል ሃገራት፡***

- ምክረሃሳብ (R201) ን በህጎች፣ በፖሊሲዎች፣ በጋራ ስምምነቶች እና በሌሎች እርምጃዎች በኩል ተግባር ላይ ማዋል አለባቸው፤
- እነዚህን እርምጃዎች ከመውሰድ በፊት ከአሰሪዎች እና ከሰራተኞች ጋር መማከር፤
- ከሌሎች ሃገሮች ጋር እና በአንዳንድ ጉዳዮች በኤምባሲዎቻቸው በኩል መስራት።

**Women in Informal Employment: Globalizing and Organizing (WIEGO)** ለድሃ ሰራተኞች፣ በተለይም ሴቶች በኢመደበኛ ኢኮኖሚ ውስጥ ስራ እንዲያገኙ አትኩሮ የሚሰራ አለም አቀፍ ኔትወርክ ነው። ሁሉም ሰራተኞች እኩል የሆነ የኢኮኖሚ እድሎች እና መብቶች ሊኖራቸው ያስፈልጋል ብለን እናምናለን። WIEGO ለውጥን የሚያመጣው በኢመደበኛ የሰራተኛ ድርጅቶች አቅም ግንባታን በመስራት፣ ስለ ኢመደበኛ ኢኮኖሚ የእውቀት ቋቱን በማስፋት እና የአካባቢ፣ ብሄራዊ እና አለም አቀፍ ፖሊሲዎች ላይ ተጽእኖ በማድረግ ነው። **www.wiego.org** ን ይጎብኙ።

**The International Domestic Workers Federation (IDWF)** አባልነት የሚያስፈልገው የቤት ውስጥ ሰራተኞች ድርጅት ነው። የቤት ውስጥ ሰራተኛ ማለት በቅጥር ግንኙነት በቤት ውስጥ ስራ ላይ ያለ ማንም ሰው ማለት ነው። IDWF የሚያምነው የቤት ውስጥ ስራ፣ ስራ እንደሆነ እና ሁሉም የቤት ውስጥ ሰራተኞች እንደ ሌሎች ሰራተኞች ተመሳሳይ መብቶች አላቸው። አላማውም መብታቸውን በሁሉም ቦታ ለመጠበቅና ለማሻሻል፣ ለቤት ውስጥ ሰራተኞች ጠንካራ፣ ዲሞክራሲያዊ እና የተባበረ አለም አቀፋዊ ድርጅት መገንባት ነው።

ሴክሬቴሪያት: c/o CTU Training Centre, 18, Shek Lei Street, Kwai Chung, N.T, Hong Kong ድረገጽ:

**www.idwfed.org**

ኢሜይል: info@idwfed.org